ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ

Wisdom at the source of the Blue Nile

# ናይል

# THE NILE





ኢ-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

ናይል 3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 12፣ ጥር 2008


## የትምህርት ጥራት በራዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)

## “ነፃ አውጪው” ማን ነው?

### ቅኝ ገዢ፣ ነፃ አውጪ መሆን ይቻለዋልን?

ጀማል ሙሀመድ (ዶ/ር)

## የውጭ ግንኙነት ሥራዎቻችን በወፍ በረር

## ህልም እልም

ቤተልሄም ሃይለማርያም

## የምክርና ድጋፍ አገልግሎት አስፈላጊነት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም


Photo Gallery page 16


## እንግሊዘኛ ቋንቋን በተለየ መንገድ ለማስተማር የሚያስችል ስምምነት ተፈረመ

በሂሩት አድማሱ



ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ እንግሊዘኛ ቋንቋን ለአፀደ ህፃናት ተማሪዎች በተለየ መንገድ ለማስተማር የሚያስችል ስምምነት ሄለን ዶሮን ከተባለ ድርጅት ጋር ተፈራረመ፡፡

የስምምነቱ ዓላማ ሄለን ዶሮን በተባለ የትምህርት ተቋም ተፈትሸው በተግባር ላይ የዋሉ እንግሊዘኛ ቋንቋን በቀላሉ መማር የሚያስችሉ ሥነ-ዘዴዎች በባሕር ዳር ከተማ ባሉ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ለመተግበር ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲውን በመወከል ስምምነቱን የፈረሙት የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሙዩኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍቅረሠላም ጋረድ ስምምነቱ አፀደ ህፃናትን ለማስተማር ፋይዳው የጎላ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የሄለን ዶሮን የትምህርት ተቋም ባለቤት ሚስስ ሄለን ዶሮን ህፃናት በቀላሉ እንግሊዘኛ ቋንቋን ለማስተማር የሚያስችለውን ስነዘዴ በ35 ሀገራትና በ900 ማዕከላት ተተግብሮ ውጤታማ መሆኑን ገልፀው ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የሚሰሩት ሥራ ስኬታማ እንደሚሆን እምነታቸውን ተናግረዋል፡፡



የሴት ተማሪዎች የሂሳብ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና የሳይንስ ትምህርታቸውን ማዳበር የሚያስችል STEM CAMP ሲካሄድ

እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

### Core Values

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility


# ናይል ጋዜጣ

**በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት**
**የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል**
**የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ**



**የአማካሪ ቦርድ አባላት**

ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
አቶ እምቢያለ በየነ
አቶ አማረ ካሳው
አቶ በላይነህ ወርቁ
ዶ/ር አልማዝ ጊዜው
አቶ ፈታሒ በቃሉ
ወ/ሮ መድኃኒት በላቸው
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢ**
ሂሩት አድማሱ

**ግራፊክስና ሌይአውት፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ፎቶ አንሺዎች፡-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**ዘጋቢዎች፡-**
የማነ ገብሩ
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትዕግስት ዳዊት
አበባ ሐብቱ
ሙሉጎጃም አንዷለም

**አምደኞች፡-**
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ጀማል ሙሀመድ (ዶ/ር)
ሞገስ አብርሃ
ደስታ ተከስተ

ቤተልሄም ሃይለማርያም
ታምሩ ከፈለኝ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ፡-**
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ
ፋንታነሽ ላቀው

**ትራንስፖርት፡-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች፡-**
ንብረት ታፈረ
ይርጋ ሻረው
አለምነሽ ሙሉ



ስልክ፡- +251 583206088
+251 583207023 A

## ርዕሰ-አንቀጽ

# አለም አቀፋዊ ግንኙነት ላይ የተጀመሩ ሥራዎችን የመደገፍ ሥራ ይቀጥል!!!

ዩኒቨርሲቲያችን ባለፉት 50 በላይ ዓመታት በሀገሪቱ በመካከለኛና ጀማሪ የቴክኒክ ባለሙያዎች በማሰልጠን ለሀገራዊ የተክኖሎጂ ሽግግርና ውጤታማ መሻሻል የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ተቋሙ የቴክኖሎጂ ትሩፋቶችን ከመጠቀም እስከ ማላመድ ባለው ሂደት ትልልቅ ፋብሪካዎች ላይ በተለያየ ደረጃ የሚሠሩ ባለሙያዎች በማፍራት ሃገራዊ ግንባታ ላይ አሻራውን አሳርፏል፡፡ እያሳረፈም ይገኛል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የሚያስተምሩ ታዋቂ የሥነ-ትምህርት ባለሙያዎችንም አፍርቷል፡፡

ከቅርብ አመታት ወዲህ የስልጠና ዘርፎችን በማስፋፋት፣ የምርምር ዘርፎችን በመለየት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን በመደገፍ በማህበረሰብ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት እየሠራ ይገኛል፡፡ ሀገሪቱን ወደ ከፍታ ማማ ለመውሰድ በሚደረገው ትንቅንቅ ላይ ትውልድን የማነፅ፣ የተለወጠ ሀገር ለመጪው ትውልድ የማስተላለፉን ትግል ይደግፋል፡፡

በሃገሪቱ የተጀመሩ ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሚጠይቁት የቴክኖሎጂና የተማረ የሰው ኃይል የማልማቱ ሃገራዊ አደራ የተጣለው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ነው፡፡ የዕድገትና የብልፅግና ሽግግር ሃገራዊ ዕቅድ ትኩረት ከሰጠባቸው ዘርፎች ውስጥ ትምህርት ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ የዕውቀት፣ የክህሎት፣ ቴክኖሎጂን በመጠቀም፣ በማላመድና ተግባር ላይ የማዋሉና ለድህነት ትግሉ አጋዥ በሆነ ሁኔታ መፈፀም እንዳለበት ይታመናል፡፡ ግዙፍ ሃብትና የላቀ ዕውቀት የሚጠይቁትን ከሌሎች መሰል ተቋማት ጋር የማፈላለጉን ሥራ መሥራት ይጠይቃል፡፡ በዚህ ረገድ ዩኒቨርሲቲያችን የመምህራንና የተማሪዎችን አቅም ለመገንባት፣ ተቋማዊ አቅም ለመፍጠር፣ አዳዲስ ዕውቀቶችና አስተሳሰቦች፣ ልምዶች በሳይንሳዊ መንገድ ተቀምረው ለሃገራዊ ልማት እንዲውሉ ለማድረግ ተግቶ እየሠራ ይገኛል፡፡

በተያዘው የመጀመሪያ ስድስት ወራት ብቻ15 ከሚልቁ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በጉድኝት በመሥራት የአጭር ጊዜ፣ የረጅም ጊዜ፣ የምርምር፣ የዕውቅና ቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎችን እየሠራን እንገኛለን፡፡ በሃገር ውስጥም ከበርካታ ተቋማት ጋር በስልጠና፣ በምርምር፣ በማማከርና አዳዲስ የተፈጠሩ ሶፍትዌሮች የተለያዩ ሥራዎችን እንዲያቀላጠፍ ተጠንተው፣ ተፈትሸው ወደ ተግባር እየተቀየሩ የኃብት ፈጠራ ምንጭ እየሆኑ ነው፡፡

የተፈጠሩ ስምምነቶች በተለይ ከሀንጋሪ፣ ከብራዚል፣ ከቻይና ከኩባ ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረጉ ግንኙነቶች ሲሆኑ ትኩረታቸው በሁለተኛና ሶስተኛ ድግሪ ተማሪዎችን ልውውጥ ለማድረግ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲመጣ እየሰራ ነው፡፡ የጋራ ተጠቃሚነትን ማዕከል ባደረገ መልኩ የዓለም አቀፍ ዩኒቨርሲቲዎች ማህበር እና የአፍሪካ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ተቋማት ማህበር አባል በሆኑ በአቅም ግንባታ ተቋሙን አለም አቀፋዊ ለማድረግ፣ ለልዩ ልዩ አካዳሚያዊ ጠቀሜታዎች ከግምት በማስገባት ባሳለፍነው ወር አባል በመሆን በቅርበት መስራት ተጀምሯል፡፡ ዓለም አቀፍ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲው መጥተው እንዲማሩ ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች ከሀገራቸው አልፈው በተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ውስጥ ገብተው እንዲሰሩና ሃገራቸውን እንዲጠቅሙ ለማድረግ የሚያስችል አሠራር ለመዘርጋት ሥራዎች ተጀምሯል፡፡

በዩኒቨርሲቲ ደረጃም አለም አቀፍ ፕሮጀክቶችን በማወዳደር የኃብት፣ የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲመጣ ትርጉም ባለው መልኩ በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ በቤልጂየም መንግስት የሚደገፍ ፕሮጀክት ዩኒቨርሲቲያችን በዚህ ዓመት አሸንፏል፡፡ ከኖርዌይ ሃገር ካሉ ተቋማት ጋርም ከሶስት በላይ ፕሮጀክቶች ተሰርተው ለውድድር ተልከዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ዓለም አቀፍ ግንኙነቱን በማጠናከር በምርምር፣ ማህበረሰብ አገልግሎትና በመማር ማስተማሩ ያሉ ሥራዎች በማሻሻል ሃገርን የመለወጥ ሥራውን አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

### ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

በናይል ጋዜጣ ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 512 በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

## ቁልፍ መልዕክት

# የትምህርት ጥራት በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

ትምህርት የምንማረው ወይም የምናስተምረው ምን ውጤት ለማግኘት ነው ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ እይታዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እንደ ሀገሮች ባህል፣ ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የሚሰጠው መልስ ይወሰናል፡፡ ይህ አጭር ጽሑፍ ትምህርት ለምን ለሚለው ጥያቄ ጥራት ያለው ትምህርት በራዕይ ጥበብ 2017 እንዴት እንደሚገለጽ በማቅረብ ማስተማር ወይም መማር ለምን ለሚለው ጥያቄ የራዕይ ጥበብ 2017ን እይታ በመግለጽ በዩኒቨርሲቲያች ማህበረሰብ ውይይት እንዲደረግ መነሻ ሀሳብ ለማቅረብ ይሞከራል፡፡

በትምህርት ልናስጨብጥ ወይም ልንጨብጥ የምንፈልገው ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ተብለው ሊቀመጡ እንደሚችሉ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የምናስተምርም ሆነ የምንማር ሰዎች በዘርፉ ያለውን ዕውቀትና ክህሎት በሚገባ መገንዘባችንና መገንባታችንን ማረጋገጥ ይገባናል፡፡ በዚህም መሠረት አንድ የሂሣብ ተማሪ በተማራቸው ኮርሶች የተካተቱትን የሂሣብ ዕውቀት በመገንዘብ ሂሣቡንም የመስራት ክህሎት መኖሩን ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ በዚህ እይታ ዕውቀት ላይ የተመሰረቱ ክህሎት የመጨበጡ ጉዳይ ወሳኝ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ መምህራን የማስተማር ዕቅድ ሲያወጡ በተማሪዎች ሊያሰርፁ የፈለጉትን ዕውቀትና ክህሎት ለይተው በሚለካ መንገድ ማስቀመጥና ካስተማሩም በኋላ ራሱን የመለካት ጉዳይ ወሳኝ ነው፡፡ በሁሉም የትምህርት ዘርፎች ተማሪዎች ሊይዙት የሚገባ ዕውቀትና ክህሎት የመለየትና ራሱን ለማስጨበጥ የመስራትና መጨበጡን የማረጋገጥ ጉዳይ ጉልህ ጥራት ያለው ትምህርት የማረጋገጥ ስራችን ነው፡፡ በመሆኑም የራዕይ ጥበብ 2017 የመጀመሪያ ውጤት በተማሩበት ዘርፍ በቂ ዕውቀትና ክህሎት የጨበጡ ተማሪዎችን ማፍራት ነው፡፡ በመሆኑም ይህን የማረጋገጥ ጉዳይ ወሳኝ የራዕዩ የስትራቴጂ ውጤት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ተማሪዎች፣ መምህራንና አመራሮች በጋራ ልንረባረብበት ይገባል፡፡ በሂሣብ ተመርቆ ወሳኝ የሚባሉ የሂሣብ ዕውቀትና ክህሎት የሌለው፣ ቋንቋ ተመርቆ በተመረቀበት ቋንቋ መፃፍና ማንበብ በሚገባ የማይችል፣ ምህንድስና ተመርቆ መሠረታዊ ዲዛይን መስራት የማይችል፣ ግብርና ተመርቆ በተግባር ሊታይ የሚችል ክህሎት ያልገነባ ተመራቂ ልናፈራ አይገባም፡፡

በቂ ዕውቀትና ክህሎት የጨበጡ ምሩቃን ማፍራት የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ለምን ጥያቄ መልስ ነው፡፡ ነገር ግን ትምህርት በዚህ የመጀመሪያ ደረጃ ውጤት ላይ የተመሰረተና ሀገር የሚለውጥ ውጤት አለው፡፡ እሱም ምሁራዊ ባህሪ ያለው ወይም ያላት ዜጋ የማፍራት ጉዳይ ነው፡፡ ዕውቀትና ክህሎት እንዲሁ ስለያዝናቸው በራሳቸው ጥቅም የሌላቸው በቀን ተቀን የተግባር ስምሪት እነሱን በመተንተን ድርጊታችንን ምሁራዊ በሆነ አግባብ ስንፈጽም ነው ጠቀሜታ ላይ የሚውሉት፡፡ በመሆኑም የትምህርት ትልቁ ግብ በራሳችን ላይ በቀን ተቀን ድርጊታችን በመግለጽ አግባብ የሚመጣውን ምክንያታዊነትንና ሳይንሳዊነትን የማረጋገጥ ላይ ያለመ ነው፡፡

በዚህም መሠረት ማን ነው የተማረ ሰው? ብለን ጥያቄ ብንጠይቅ መልሱ ድርጊትንም ሆነ የሚሰጠውን ሀሳብ በዕውቀት ላይና በዕውነተኛ መረጃ ተመስርቶ ነገሮችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመተንተን የሚረዳ ሰው ነው፡፡ በዚህ ዕይታ ኢትዮጵያ ስንት የተማረ ሰው አላት ብለን በመጠየቅ ልንወያይ ይገባል፡፡

በራዕይ ጥበብ 2017 ጥራት ያለው ትምህርት እናረጋግጥ ስንል የመጀመሪያ ደረጃ ውጤት የሆነውንና ዕውቀትና ክህሎት ማስጨበጥ ላይ ያለመውን ዕቅድ በማሳካትና እሱን እንደ ዋነኛ መደላደል በመጠቀም የትምህርትን ዋነኛ ግብ ማለትም ምሁራዊ ባህሪ ያላቸው ዜጎች ማፍራት ላይ ያለመ ነው፡፡ በመሆኑም ትልቅ ርብርብ የሚጠይቅ ስለሆነ ሁላችንም ለስኬታማነቱ በርትተን እንስራ፡ በራዕዩ እሳቤዎች ላይም ተከታታይነት ያለው ውይይት እናድርግ፡፡

ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!

To follow the latest news about BDU,
check out our website:-
**http://www.bduinfo63@bdu.edu.et**
**or**
**http://www.bdu.edu.et**
facebook page:- **www.facebook.com/bduethiopia**

# ዜና ትንታኔ

## ዩኒቨርሲቲው በማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች የ3ኛ ዲግሪ ሊከፈት ነው

በታድዬ አስማሪ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከጀርመኑ ዊልሜየር ዩኒቨርሲቲ ጋር በማይዳሰስ የባህል ቅርሶች ላይ በጋራ ጥናት እና ምርምር ለማካሄድ እንዲሁም የ3ኛ ዲግሪ መርኃ ግብር ለመጀመር ሚያስችላቸውን ሲምፖዚየም አካሄዱ። ሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች የምርምር ሥራዎችን እና የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በጋራ በመቅረፅ የጋራ ተጠቃሚ መሆኑን ተገልጿል።

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ እንደተናገሩት ዩኒቨርሲቲውን የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ በሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ በርካታ መርኃ ግብሮችን ለጥናት እና ምርምር ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እና በጀት በመመደብ ምሁራን እንዲሳተፉ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል። መምህራን የምርምር ሥራቸውን ወደ ማህበረሰቡ በማስረፅ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የተለያዩ ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ሲምፖዚየም እና ጉባዔዎችን በማዘጋጀት የምርምር ሥራዎች ወደ ተግባር እንዲቀየሩ እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል። ዶ/ር ማተቤ አክለውም የሀገራችን የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች በጥናትና ምርምር እየተደገፉ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ትኩረት ባለመሰጠቱ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርስ ላይ የሶስተኛ ዲግሪ መርኃ ግብር መክፈት የጀመረውን ጉዳና አንድ ርምጃ ከፍ ስለሚያደርገው መድረኩ መዘጋጀቱ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ፕሮፌሰር ቲያጐ ዲ አልቬራ ፒንቶ የጀርመኑን ዊልሜየር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት መልዕክት ባስተላለፉበት ወቅት እንደተናገሩት ኢትዮጵያ የበርካታ የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች ባለቤት በመሆኗ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች ላይ ጥናትና ምርምር ለማካሄድ ዩኒቨርሲቲያቸው በተግባር እንደሚንቀሳቀስ ገልፀዋል። በባህላዊ ሙዚቃ ጥናትና አመዘጋገብ ዘዴ፣ በፊልም ሥራ ቴክኒክ፣ በባህላዊ ሙዚቃ መሣሪያ ጥናት አብሮ ለመሥራት ስምምነት የተደረሰ ሲሆን ወደፊትም በባህላዊ ቅርስ አስተዳደር እና በሚዲያ ቴክኖሎጂና ፍልስፍና አብሮ ለመሥራት ፍላጐት እንዳላቸው ገልጸዋል።

ዊልሜየር ዩኒቨርሲቲ የመምህራንን አቅም ለመገንባት አጫጭር የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ የልምድ ልውውጥ በማድረግ እንዲሁም ለተማሪዎች ለምርምር ሥራቸው ተጨማሪ ግብአት እንዲሆናቸው በጀርመን የተሰሩ የምርምር ሥራዎችን እንዲያገኙ እንደሚያደርግ ፕሮፌሰር ቲያጐ ገልጸው በዩኒቨርሲቲው የሙዚቃና የፊልም ቤተሙከራ ከነሙሉ መማሪያው፣ የባህል ቅርሶች ቤተ መዛግብት በማቋቋም ጥናትና ምርምሩ ተጠናክሮ እንዲካሄድ ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል።

በዌልሚየር ዩኒቨርሲቲ የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርስ ጥናት መምህርና ተመራማሪ የሆኑት ዶ/ር ጌቴ ገላዬ ዩኒቨርሲቲው በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርስ የሶስተኛ ዲግሪ መርኃ ግብር ሲከፈት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን በማሟላት ድጋፍ ከማድረግ በተጨማሪ ሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች በተስማሙበት አጫጭር ስልጠናዎች፣ የተለያዩ ወርክ ሾፕ እና ሲምፖዚየም ማዘጋጀት፣ የተለያዩ ኮንሰርቶችን በጀርመንም ሆነ በኢትዮጵያ ማዘጋጀት እንዲሁም የምርምር ሥራዎችን በጋራ እንዲሰሩ ያደርጋል ብለዋል።

ዶ/ር ገድፍ አበዋ የሶሻል ሳይንስ ፋኩልቲ ዲን ዊልሜየር ዩኒቨርሲቲ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር የማንነታችን እና የስልጣኔያችን መገለጫ በሆነው በማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርስ ላይ በጋራ ለመሥራት በሚያደርገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደርና ማህበረሰብ ከፍተኛ ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል።

በሲምፖዚየሙ ላይ አባይ የባህልና ልማት ጥናትና ምርምር ማዕከል እና በሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ የፎክሎር (የባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል ኃላፊዎች የየክፍላቸውን ዓላማና ተግባር በሲምፖዚየሙ ያቀረቡ ሲሆን በተለይ የፎክሎር ትምህርት ክፍል ተጠሪ ዶ/ር ዋልተንጉስ መኮንን ትምህርት ክፍሉ የሶስተኛ ዲግሪ መርኃ ግብሩን በአፋጣኝ ለማስጀመር ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል ብለዋል። የአባይ የባህልና ልማት ጥናትና ምርምር ማዕከል ዳይሬክተር ዶ/ር ሙሉቀን ገረመው በክፍላቸው የተጠኑ የባህልና ቅርስ ጥናት የምርምር ስራዎችን በመግለፅ የምርምር ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጠል ገልጸዋል። በሲምፖዚየሙ ላይ ተሳታፊዎች የተለያዩ ጥያቄዎች አንስተው ሰፊ ማብራሪያ ተሰጥቷል።

## ቫይረሱ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ 12 ሚሊዩን ሰዎች ህይወታቸው ማለፉ ተገለጸ

በታድዬ አስማሪ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኤችአይቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዳይሬክቶሬት 27ኛውን የዓለም ኤችአይቪ ኤድስ ቀን በዩኒቨርሲቲው አዳራሽ «አንድም ሰው በኤች አይ ቪ/ኤድስ እንዳይያዝ ሀላፊነታችን በመወጣት የሀገራችንን ህዳሴ እናሳካ» በሚል ሀገር አቀፍ መሪ ቃል በፓናል ውይይት አከበረ።

የዩኒቨርሲቲው ኤችአይቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዳይሬክቶሬት ሲስተር ማርታ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

## የርቀት ትምህርት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ተጨማሪ የሥራ ፈቃድ ተሰጠው

በታድዬ አስማሪ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የርቀት ትምህርት መርኃ ግብር ዩኒቨርሲቲው ከሚሰጣቸው መደበኛ፣ ተከታታይ እና የክረምት ትምህርት መርኃ ግብሮች መካከል አንዱ ሲሆን የርቀት ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ በ1998 የተለያዩ የማስተባበሪያ ማዕከላትን በመክፈት በቦታ ርቀትና በሥራ አለመመቻቸት ምክንያት መማር ላልቻሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙ እያደረገ ይገኛል። በርቀት ትምህርት ጽ/ቤቱ በአስር አመት ጉዞው መማር እየፈለጉ በተለያዩ ችግሮች መማር ላልቻሉ በርካታ ዜጐች የመማር ፍላጐታቸውን አሟልቷል።

የርቀት ትምህርት ጽ/ቤቱ ዜጐች በቅርበት እንዲማሩ በማለት የቅርንጫፍ ማስተባበሪያ ማዕከላትን በመክፈት ባሕር ዳርና ጨምሮ በአዲስ አበባ፣ በጐንደር፣ በወልዲያ፣ በደሴ፣ በደብረብርሃን፣ በደብረማርቆስ ከተማና አጐራባች ወረዳዎችን መሰረት በማድረግ መማር ለሚፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። እነዚህ ማዕከላት በቅርቡ የከፍተኛ ትምህርት ጥራት የደረጃዎች ምዘና በኩል በተካሄደው የባለሙያዎች ጉብኝት ተጨማሪ የሥራ ፈቃድ የተሰጠው ሲሆን የርቀት ትምህርቱ አሰጣጥና የማዕከላት አደረጃጀት አበረታች መሆኑ በባለሙያዎች ተገልጿል።

በየከተማው የሚገኙ ማዕከላት ማለትም የጐንደር ማዕከል በጐንደር መምህራን ኮሌጅ፣ የወልዲያ ማዕከል በወልዲያ መምህራን ኮሌጅ፣ የደሴ ማዕከል በደሴ መምህራን ኮሌጅ፣ በደብረ ብረሃን ማዕከል በደብረብርሃን መምህራን ኮሌጅ በአዲስ አበባ በ2ኛ ደረጃ ት/ቤት እና በደብረማርቆስ በደብረማርቆስ መምህራን ኮሌጅ ውስጥ በአነስተኛ ክፍያ ቢሮዎችን ያገኙ ሲሆን ለኮሌጆቹ ሁለት ሠራተኞች የትምህርት እድል ይሰጣል። በማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ እና በተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎች በተደረገ ስምምነት ተቋሙ ለማስተባበሪያ ማዕከላቱ አገልግሎት የሚውል የተለያዩ ክፍሎችን የሚሰጥ ሲሆን ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ በየአመቱ በተቋሙ ኃላፊዎች ተመልመለው መስፈርቱን ላሟሉ ሠራተኞች የትምህርት እድል በመስጠት ላይ ነው።

የቅርንጫፍ ማስተባበሪያ ማዕከላቱ በስራቸው የአይሲቲ፣ የቤተ መፃህፍት፣ የምዝገባና የሞጁል ስርጭት ክፍሎችን በመክፈት ሰፊ ስራ እየሰሩ ይገኛል። ዋና የርቀት ትምህርት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ለእያንዳንዱ ማዕከል ኮምፒውተሮች፣ መፃህፍትና የማንበቢያ ወንበርና ጠረጴዛ በማሟላት ተማሪዎች እንዲገለገሉበት ተደርጓል። ሞጁል በወቅቱ ለተማሪ እንዲደረስ ቀድሞ በማዘጋጀትና በመላክ እጥረት እንዳይከሰት እየተደረገ ነው። ለነዚህ ክፍሎች ባለሙያዎችን በመቅጠር የኢንተርኔትና የኮምፒውተር አገልግሎት ለሚፈልጉ የአይሲቲ፣ የቤተ መፃህፍት እንዲሁም የምዝገባና የፋይል አያያዝ ስራዎችን በመስራት ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ተጠቃሚውን እያረካ ይገኛል። በተለይ የአይሲቲ እና ቤተ መፃህፍቱ አደረጃጀት ተማሪዎቹ የመመረቂያ ፁሁፋቸውን እንዲሰሩ የሚያግዛቸው ሆኖ የተዘጋጀ ሲሆን የኢንተርኔት አገልግሎት እና በቤተ መፃህፍቱ ውስጥ የተለያዩ መፃህፍትን በማሟላት ተማሪዎች የምርምር ሥራቸውን ሳይቸገሩ እንዲሰሩና እንዲጠቀሙበት ለአገልግሎት ክፍት ተደርገዋል። ተማሪዎች ዋናው ጽ/ቤት መምጣት ሳያስፈልጋቸው ማስረጃዎቻቸውን በፈለጉ ጊዜ እንዲያገኙ የሚያደርግ ስርዓት ተፈጥሮ ፋይላቸው በስርአት ተደራጅቶ ያለምንም ችግር ማስረጃ እንዲጠይቁና እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል።

በአሁን ሰአት በየቅርንጫፍ ማዕከላት ትምህርታቸውን እየተከታተሉ የሚገኙ ተማሪዎች በርካታ ናቸው። በዚህም ባሕር ዳር 3277፣ በጐንደር ማዕከል 1999፣ በወልዲያ ማዕከል 2919፣ በደሴ ማዕከል 2085፣ በደብረብርሃን ማዕከል 600 በላይ፣ በደብረ ማርቆስ 1476 እንዲሁም በአዲስ አበባ ማዕከል 2914 ተማሪዎች ሲሆን በየማዕከላቱ እየተማሩ ከሚገኙ ተማሪዎች መካከል ቁጥራቸው ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ደግሞ ሴቶች ናቸው። የሴቶች ተሳትፎ ከፍተኛ መሆን ሴቶችን በማስተማር የኢኮኖሚው ተጠቃሚ የማድረግ ሀገራዊ ድርሻውን እየተወጣ ይገኛል።

ከዚህ በተጨማሪ ጽ/ቤቱ የተማሪዎች የትምህርት መርጃ መሳሪያ የሆኑት ሞጁሎች በወቅቱ ወደ የማዕከላቱ በመላክ ተማሪዎች የሞጁል እጥረት እንዳይገጥማቸው የሞጁል ክፍል አዘጋጅቶ ወደ ስራ ገብቷል። ጽ/ቤቱ በየአመቱ የሚያዘጋጀው ካሌንደር ሲኖረው በምዝገባ ወቅት ለተማሪዎች ከሚሰጣቸው ሞጁል ጋር ካላንደሩ ስለሚሰጣቸው የማጠናከሪያ ትምህርቱም ሆነ የፈተና ጊዜ በቀላሉ ቀድመው እንዲያውቁት ይደረጋል። በተጨማሪም የማካካሻ ትምህርት የሚሰጥበትና የፈተና ቀን ሲደርስ ጽ/ቤቱ ቀደም ብሎ በሬዲዮና ቴሌቪዥን የማሳወቅ ሥራ ይሰራል። በማዕከላቱ የአሰራር ችግር ካጋጠመ ጽ/ቤቱ የሚያወቅበትና አሰራሩን የሚገመግምበት የአስተያየት መስጫ ሳጥን በየማዕከሉ የተቀመጠ ሲሆን በየጊዜውም የተሰጡ አስተያየቶች እየተገመገሙና እየተፈተሸ ምላሽ ይሰጥበታል።

# አበይት ዜናዎች...

## 'የርቀት ትምህርት ከየት ወደየት?' በሚል ርዕስ ስምፖዚየም ተካሄደ

በትዕግስት ዳዊት

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የርቀትና ተከታታይ ትምህርት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት 'የርቀት ትምህርት ከየት ወደየት?' በሚል ርዕስ አገር አቀፍ አውደ ጥናት አካሄደ፡፡

የዩኒቨርሲቲው የርቀትና ተከታታይ ትምህርት ዳይሬክተር አቶ መሰረት አድነው እንደተናገሩት ጽ/ቤቱ ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት ሁኔታዎችን እያመቻቸ መሆኑን ገልጸው የድህረ ገፅ አገልግሎት እና ዘመናዊ የተማሪዎች መረጃ ማጠናቀሪያ ዘዴ የኢ-ለርኒግ ዝግጅቱን አጠናቆ በቀጣዩ ወሰነ ትምህርት ወደ ተግባር እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ በመክፈቻ መርኃ ግብሩ ላይ ዩኒቨርሲቲው የትምህርትን ተደራሽነትን ለማረጋገጥ በሰው ሀብት ልማት ላይ እየሠራ መሆኑን ገልፀው በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት የተገነባ ትውልድ ለማፍራት የተለያዩ ሲምፖዚየሞችን በማዘጋጀት መወያየት አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በሲምፖዚየሙ ላይ 'የርቀት ትምህርት የደረሰበት ደረጃ እና የወደፊት አቅጣጫ ተሞክሮዎች' በሚል ርዕስ በአቶ አስናቀ ታረቀኝ ጥናታዊ ፅሑፍ የቀረበ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው የርቀት ትምህርት ሲከፈት ዋና አላማ የነበረው በቀን ሊማሩ ለማይችሉና ተደራሽነት ላልነበራቸው በርቀት ያሉ ሰዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲሁም ለዩኒቨርሲቲው አንድ የገቢ ምንጭ ለመፍጠር መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ በቀረቡ ጹሑፎች ላይ ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች ትኩረት እንዲሰጥባቸው ተጠቁሟል፡፡
ዶ/ር ማተቤ ታፈረ ከጽ/ቤቱ ጋር አብረው የሰሩና ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉ አካላት የምስክር የምስጋና ወረቀት ከሰጡ በኋላ ከትምህርት ጥራትና አግባብ ኤጀንሲ (HERQA) የመጡትን መስፈርቶች በማሟላትና በማጽደቅ የበለጠ ድጋፍ እንዲያደርጉ አሳስበዋል፡፡
ጽ/ቤቱ በባሕር ዳር፣ በደብረ ማርቆስ፣ በአዲስ አበባ፣ በደብረ ብርሐን፣ በደሴ፣ በወልዲያ እና በጎንደር ሰባት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያሉት ሲሆን በአስራ አንድ የትምህርት ዘርፎች ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ለሀገር እድገት ጉልህ ድርሻ ያላቸውን ዜጎች በማፍራት ላይ ይገኛል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በርቀትና ተከታታይ ትምህርት ከ1998 እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ከ20,000 በላይ ተማሪዎችን ያስመረቀ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ሰላሳ አምስት ከመቶ ሴቶች መሆናቸው ታውቋል፡፡

## ለሴት ተማሪዎች STEM CAMP ተዘጋጀ

በትዕግስት ዳዊት

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ከሂሳብ ት/ክፍል ጋር በመተባበር ለሴት ተማሪዎች የሂሳብ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና የሳይንስ ትምህርታቸውን እንዲያዳብሩ የሚያስችል STEM CAMP አካሄደ፡፡

የባሕር ዳር ሳይንስ ኢንኩቤሽን ማዕከል (STEM) ከ9ኛ-11ኛ ክፍል ላሉ ከተለያዩ ት/ቤቶች ለተውጣጡ ከ50 በላይ ለሚሆኑ ሴት ተማሪዎች ለሰባት ተከታታይ ቀናት ካምፕ ውስጥ በማስገባት የሂሳብ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና የባዮሎጂ ትምህርታቸውን እንዲያዳብሩ ታስቦ የተዘጋጀ ስልጠና መሆኑን የማዕከሉ ዳይሬክተር አቶ ብሬ ጌጤ ተናግረዋል፡፡ አቶ ብሬ ተማሪዎቹን ማሰልጠን ያስፈለገበትን ምክንያት ሲያስረዱ ከመደበኛው ካሪኩለም የተለየ እና ለተማሪዎች የአእምሮ መነቃቃት እና አዳዲስ ግኝቶችን እንዲያመጡ ለማስቻል እንዲሁም ተማሪዎቹ ያላቸውን ተሰጥኦ እና የፈጠራ ችሎታ ተጠቅመው ብቁ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡

አቶ ብሬ አክለው እንደተናገሩት የሴቶች ካምፕ ሴቶች በሳይንስ ዙሪያ ልዩ ግንዛቤ እንዲያገኙ እንደሚረዳቸው ገልጸው ይህ ካምፕ ለሴቶች ሲዘጋጅ የመጀመሪያ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ተማሪዎቹ በሳይንስ፣ በሂሳብ፣ በኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ ትምህርቶች ዙሪያ ልዩ ትኩረት እንዲያገኙና የማዕከሉ የወደፊት ዓላማም ተማሪዎችን የወደፊት ሳይንቲስቶች እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ ወደፊትም ማዕከሉ በየትምህርት ቤቱ ክትትል እንደሚያደርግና ወደፊት ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ገብተው ተሰጥኦዋቸውን እንዲያዳብሩ ጥረት ያደርጋል ብለዋል፡፡

የሂሳብ ት/ክፍል መምህር አቶ ሙላት ገበየሁ ዝግጅቱ ለተማሪዎቹ ከመደበኛው ሥርዓተ ትምህርት በተጨማሪ በንድፈ ሀሳብ የተማሩትን በተግባር እንዲያከናውኑት፣ ለሂሳብ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት እንዲቀይሩ፣ ሁሉም ሳይንስ ሂሳብ ነው የሚለውን በተግባር እንዲያዩት ያግዛቸዋል ብለዋል፡፡

አንዳንድ ሰልጣኝ ተማሪዎች በበኩላቸው በቆይታቸው ሳይንስን በጨዋታ መልክ በመማራቸው በሳይንስ ዙሪያ ልዩ ግንዛቤ እንዳስገኘላቸው፣ የሳይንስ ትምህርት በውስጣቸው እንዲሰርፅ እንደረዳቸውና ትምህርትንና ጨዋታን በማገናኘት በሳይንስ፣ በሂሳብ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ትምህርቶች ላይ በቂ ልምምድ በማድረጋቸው ትምህርቱ ቀላል እንዲሆንና ሲማሩትም ለአረዳድ የበለጠ እንደሚያግዛቸው አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

To follow the
latest news about BDU, check out our website፡-
**http://www.bduinfo63@bdu.edu.et**
**or**
**http://www.bdu.edu.et**
facebook page:- **www.facebook.com/bduethiopia**

## የቤተ መጽሐፍት አገልግሎት አሰጣጥን በአዲስ ሶፍትዌር ዘመናዊ ማድረግ ተቻለ

በሙሉጐጃም አንዱዓለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ተቋም "የተቀናጀ የቤተ መጽሐፍት መረጃ ስርዓት (Integrated Library Service)" የተሰኘ አዲስ ሶፍትዌር በተቋሙ የመሰብሰቢያ አዳራሽ አስመረቀ፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ በተሰራው ሶፍትዌር አማካኝነት የመጽሐፍት ውሰት በማድረግ ሶፍትዌሩን የመረቁ ሲሆን አዳዲስ ሶፍትዌሮችን ከመፍጠር አንፃር ተቋሙ ፈር ቀዳጅ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ገልጸው ተቋሙ በመስራት ላይ ያለው አዲስ የዲጅታል ቤተ መጽሐፍት ሲጀምር የበለጠ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ እንደሚያደረግ ተናግረዋል፡፡ ሶፍትዌሩ በአንድ ካርድ ሁሉንም አገልግሎቶች የሚስተናገዱበት መንገድ ማመቻቸት እንዳለበት ዶ/ር ባይሌ አሳስበዋል፡፡

በተቋሙ ቤተ መጽሐፍት ዳይሬክተር አቶ ሠርፀ አበበ እና በኮምፒውቲንግ ፋኩልቲ መምህር አቶ ቻላቸው ሙሉቀን አማካኝነት የተዘጋጀዉ አዲሱ ሶፍትዌር በተለምዶ አሠራር ቤተ መጽሐፍት ውስጥ የሚሰጠውን የካታሎግ እና የዉሰት አገልግሎት በመለወጥ ተጠቃሚዎች በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ኢንተርኔትን በመጠቀም የተደራጀ የመፅሐፍት መረጃዎችን መመልከትና ዉሰት መፈጸም በሚችሉበት ሁኔታ የተዘጋጀ ነው፡፡

አቶ ሠርፀ እንደገለጹት አሁን በቤተ መጽሐፍት ውስጥ ያሉ መጽሐፍቶች ቁጥራቸው ከተጠቃሚው ጋር ስለማይጣጣም እንዲሁም መጽሐፍቶችን በህትመት መልክ ብቻ ገዝቶ ችግሩን መቅረፍ አስቸጋሪ በመሆኑ በተሰራዉ ሶፈትዌር ታግዞ በርካታ መጽሐፍትን በሶፍት ቅጂ በማሰባሰብ እና በርዕሳቸው ወይም በትምህርት ዓይነቶች በማደራጀት ሁሉም ሰው በቀጥታ መጽሐፍትን በዩኒቨርሲቲዉ የመረጃ መረብ አማካኝነት የሚያገኙበትን ዘዴ ነው፡፡ በተጨማሪም ሶፍትዌሩ በቤተ መጽሐፍት ውስጥ የሚገኙ መጽሐፍትን በሙሉ በአግባቡና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መልኩ መረጃን በተደራጀ መንገድ በመያዝ እንዲሁም በግዥ የሚመጡ መጽሐፍት በቂ ባለመሆናቸው ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ በመጠቀም የመጽሐፍት ተደራሽነትን ለመፍጠር እንደሚቻል ገልፀው የሶፍትዌሩ ስራ ተጠናቆ ወደ ተግባር የተገባ ቢሆንም ለተጠቃሚዎች ተከታታይ ስልጠና እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

## የፀረ ሙስና ቀን ተከበረ

በታድዬ አስማረ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፀረ ሙስናና ስነ ምግባር ዳይሬክቶሬት በሀገር አቀፍ ደረጃ «ህፃናትንና ወጣቶቻችን በስነ ምግባር መገንባት አገርን በመገንባት» በሚል መሪ ቃል ለ11ኛ ጊዜ የሚከበረውን የፀረ ሙስና ቀን በፓናል ውይይት አከበረ፡፡

በእለቱ የአመለካከት ለውጥ ለስነ ምግባር ያለው ሚና እና ሰዎች ለምን ሙሰኛ ይሆናሉ በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሁፍ የቀረበ ሲሆን በዩኒቨርሲቲዎች የተማሪዎች አገልግሎት አካባቢ፣ በግዥ እና ንብረት አስተዳደር፣ በሰው ኃይል አስተዳደር ክፍሎች ውስጥ የሚታዩ የዘርፍ፣ የንብረት ብክነት እና የመልካም አስተዳደር ችግር ተለይተው በግልፅ ቀርበው ሰፊ ውይይት ተደርጓል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የፀረ ሙስና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ሙሀመድ ይማም የሙስና እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንደማንኛውም ዩኒቨርሲቲ በዩኒቨርሲቲያችን ችግሮቹ እየታዩበት ያለ ሲሆን የዳይሬክቶሬት ጽ/ቤቱ የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ ከማስተማር ባሻገር የሙስና እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ምንጭ ናቸው ተብለው የተለዩ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ ችግሮቹ እንዳይከሰቱ ለማድረግ እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ ጽ/ቤቱ ማስረጃዎችን በማሰባሰብና ምርመራ እያካሄደ በተገኘው ውጤት ችግር ፈጣሪ የሆኑ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ለማድረግ እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑን ተናግሯል፡፡

በዩኒቨርሲቲው እየታዩ ያሉ የሙስና እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች በቁርጠኝነት ለመፍታት እና አጥፊዎች በሕግ የሚጠየቁበትን አሰራር

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# የውጭ ግንኙነት ሥራዎቻችን በወፍ በረር

በሞገስ አብርሃ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሰቲ በመማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት እና በቴክኖሎጂ ሽግግር መስኮች በርካታ ሥራዎችነን እያከናወነ ይገኛል፡፡

ተልዕኮዎችን ለመፈፀም የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር አጋር አካሎች ትብብር፣ ድጋፍ እና በቅንጅት መሥራት የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ለውጭ ግንኙነትና ፓርትነርሺፕ ዳይሬክቶሬት ዩኒቨርሲቲው ከተቋሙ ውጭ ካሉ ሁሉም አካላት ጋር ጉድኝት በመፍጠር የተቋሙ ተልዕኮዎች እንዲሳኩ እየተሠራ ነው፡፡ ዳይሬክቶሬቱ የውጭ መንግስታዊ ተቋማት፣ የሃገር ውስጥ ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ግለሰቦችና የንግድ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመመስረት የተቋሙ መምህራን፣ የአስተዳደር ሰራተኞች እና ተማሪዎች የዕውቀት፣ ክህሎት እና ልምዶችን በመቀመር ዩኒቨርሲቲው ሃገራችን የምትፈልገውን በአዕምሮው የዳበረ፣ በዕውቀትና በክህሎት የተገነባ መሠረታዊ ሃገራዊ ተግዳሮቶችን ለመፍታት አቅሙ የጎለበተ ዜጋ ለመፈጠር በሚደረገው ሥራ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ በመሆን አስተዋፅኦቸውን እንዲያበረክቱ የማገዝ ዓላማዎችን ያነገበ ነው፡፡

የእነዚህ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ማህበራት አባል ስንሆን እንደ ዩኒቨርሲቲ ዓለም አቀፋዊ ስምን ከፍ ያደርጋል፣ የተለያዩ ማህበራቱ በሚያሰናዱት ስልጠናዎችን መሳተፍን ያስችላል፡፡

በተያዘው ዓመት ከሃገር ውስጥ እና ከውጭ ተቋማት፣ ግለሰቦችና የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት ጋር በቅርበት በመሥራት ዩኒቨርሲውን ገጽታ የመገንባት፣ የልዩ ልዩ ልምዶች፣ ተሞክሮዎች፣ አዳዲስ አሠራሮች፣ መልካም ግንኙነቶች የመመስረት፣ ተቋሙን ዓለም አቀፋዊ ደረጃው ከፍ እንዲል ያደርጉ አዳዲስ ፕሮጀክቶች ተነድፈው ለውድድር እንዲቀርቡ የመደገፍ፣ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን የሚያጠናክሩ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በተለይ ከቻይና ከብራዚል፣ ከሃንጋሪ እና ከየተባበሩት የአረብ ኢሚሬቶች ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጠሩ ግንኙነቶች ናቸው፡፡ ከ20 በላይ አዳዲስ የዓለም ዩኒቨርሲቲዎችና ተቋማት ጋር እንዲሁም ከ5 በላይ ሃገራዊ ዩኒቨርሲቲዎችና ተቋማት ጋር እስከ ተያዘው ወር ድረስ አዲስ ስምምነቶች ተፈጥረዋል፡፡ በተጨማሪም በሂደት ላይ ያሉ ከ50 በላይ አዳዲስ ስምምነቶችን ለመድረስ እየተሠራ ይገኛል፡፡ እነዚህ ስምምነቶችን መሰረት በማድረግ በመማር ማስተማርና በምርምር፣ እንዲሁም በማህበረሰብ ተኮር ሥራዎች ላይ ወደ ተግባር የተገባና ውይይቶችና የተለያዩ ጉብኝቶች ለማከናወን ሂደቶች ተጀመረዋል፡፡ በተለይ ደግሞ ተቋሙ በከፍተኛ ሁኔታ የ2ኛ እና የ3ኛ ድግሪ የትምህርት ዕድሎችን ለማመቻቸት የሚያስችሉ ስምምነቶች እና አዳዲስ ፕሮጅክቶችን በመንደፍ ሃገራዊ ፋይዳቸው የላቁ መርኃ-ግብሮች እንዲከፈቱ የሚያስችል ሥራዎችን በመደገፍ በኩልም ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡

ኃላፊዎች፣ ተማሪዎችና መምህራን ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶችን ተሳታፊ በመሆን ባላቸው ዕውቀትና ክህሎት ተጨማሪ ዓለም አቀፋዊ ልምዶችና ተሞክሮዎችን እንዲቀስሙ ለማስቻል በአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስልጠናዎች እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

በተያዘው ዓመት ከተሠራው ሌላው ጉልህ ሥራ ውስጥ የሚመደበው በዘላቂ ጥቅም ላይ የሚያጠነጥን የዓለም አቀፍ ዩኒቨርሲቲዎች ማህበር አባል ለመሆን አስፈላጊውን መረጃ በመሰብሰብ፣ መረጃዎቹ የማህበሩን መስፈርት በሚያሟላ መልኩ በማዘጋጀት ከማህበሩ ጋር በተከታታይ በመፃፃፍ በዩኒስኮ ሥር በተቋቋመው የዓለም ዩኒቨርሲቲውች ማህበር አባል ሆነናል፡፡

በተመሳሳይ ሌላው ከአፍሪካ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ተቋማት ጥምረትን ዩኒቨርሲቲያችን በአባልነት የተቀላቀለው በዚህ ወር ነው፡፡ ምን አልባትም የእነዚህ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ማህበራት አባል ስንሆን እንደ ዩኒቨርሲቲ ዓለም አቀፋዊ ስምን ከፍ ያደርጋል፣ የተለያዩ ማህበራቱ በሚያሰናዱት ስልጠናዎችን መሳተፍን ያስችላል፡፡ ነፃ የትምርት ዕድሎችን፣ የምርምርና ድጋፍ፣ አባል ከሆኑ ተቋማት ጋር የመምህራንና ተማሪዎች ልውውጥ ለማድረግ ያስችላል፣ ለኮንፈረንስ የገንዘብ ድጋፍ ይገኛል፡፡ ከተቋማቱ የትምህርት መረጃ መሳሪያዎችን የምናገኝበት የምርምር ጆርናሎችን እና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮችን መረጃ የምናገኝበት ድልድይ ሆነው ያገለግላሉ፡፡

በሃገር ውስጥ ከሚገኙ ኤምባሲዎችና ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ በተለያየ ዓለም ከሚገኙ ኢትዮጵያ ኢምባሲዎች፣ ቆንሲላዎች ከኢትዮጵያ ማህበረሰብ ተቋማት እና ኢትዮጵያዊን ትውልደ ኢትዮጵያ እና ከውጭ ሃገራት ታዋቂ ፕሮፌሰሮች ጋር በቅርበት በመሥራት ልዩ ልዩ ፋይዳ ያላቸው ትብብሮችን መስርተናል፡፡ ሃገር ውስጥ ካሉ የንግድ ድርጅቶች፣ ፋብሪካዎች እና ልዩ ልዩ ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ምሩቃን የሥራ ዕድልና የኢንዱስትሪ ልምድ እንዲያገኙ የሚሠሩ ሥራዎች አሉ፡፡

የተቋሙ የውጭ ደንበኞችና የአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ልዩ ልዩ የምክክር መድረኮችን በመፍጠር በተቋሙ እየተከናወኑ ያሉት ሥራዎች ላይ ግንዛቤ በመፍጠር፣ ውስንነቶች ተቀርፈው ተልዕኮዎችን ለመፈፀም እንዲቻል ዩኒቨርሲቲው ግብዓት ያገኘበት አሠራሮቹን የሚፈትሽበት ዕድል ፈጥሯል፡፡

ዳይሬክቶሬቱ በመጀመሪያው 6 ወር የደንበኞች እርካታ በማሳደግ፣ ዩኒቨርሲቲውን የተለያዩ ጥምረቶችና ማህበራት አባል በማድረግ፣ በዩኒቨርሲቲው ተልዕኮዎች ዙሪያ የኃላፊዎች፣ የመምህራን፣ የተማሪዎችን ዕውቀት ክህሎት እና ዓለም ዓቀፍ ተሞክሮ በመጨመር፣ አዳዲስ ጠንካራ አጋርነቶችና ትብብሮችን በመፍጠር እና የተጀመሩትን በመከታተል በርካታ ሥራዎችን አከናውኗል፡፡ በቀረው ጊዜ ትልልቅ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የሆኑ ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸው የውጭ ግንኙነትና ፓርትነርሺፕ ሥራዎችን በማከናወን ዓመቱን በስኬት ለማጠናቀቅ ይሠራል፡፡

# የጉዞ ማስታወሻ ...

ከገጽ 10 የዞረ

ቅዝቃዜውን በመቋቋም ወደ አጥር ግቢው ውስጥ ስንገባ በእውነት እላችኋለሁ እነደዚያ ሲቀዘቅዘን የነበረው አየር የለም፡፡ ቅዳሴ ብናስጨርስ መልካም ነበር፡፡ ነገር ግን የጉዞችን ሰዓት ደርሶ ስለነበር መውጣት ግድ ሆኖብን አጭር የግል ፀሎት አድርገን ተመለስን፡፡ አልጋ በያዝንበት አቅራቢያ ከምትገኝ ትንሽ ካፌ ውስጥ ቁርሳችን በላን፡፡ ትንሽ ካፌ ስላችሁ መቼም ቁርሱ ምን ይሆን ማለታችሁ አይቀሬ ነው፡፡ ከአስተናጋጅ ልጀምርላችሁ በግምት እድሚያቸው 60 ዓመት አካባቢ የሚሆናቸው እናት ወደ እኛ ተጠግተው ‹‹ምን ይምጣላችሁ ልጆቸ›› አሉን፡፡ ‹‹ቁርስ አለ›› አልናቸው፡፡ ‹‹ሁሉም አለ ምን ይሁን?›› አሉ፡፡ አንድ እንጀራ ፍርፍርና ሁለት ሽሮ አዘዝን፡፡ ባዘዝነው መሰረት መጣልን፡፡ በተለይ እንጀራ ፍርፍሩ በጣም ይጣፍጣል፡፡ እኔ አንድ ይጨመር አልኳቸው፡፡ ብዙ ጊዜ ጭማሪ ምግብ አይጣፍጥም የእሳቸው ግን የበለጠ ጣዕም አለው፡፡ በሻይ አወራርደን ደስ ብሎን ተመግበን አመስግነን ወጣን፡፡

ወደ ቀጣዩ ጉዞ ለመሄድ ሰዓታችን መጠቀም ግድ ነው፡፡ ወደ መኪናችን ስናመራ ሹፌሩ ለመሄድ ተዘጋጅቶ ጠበቀን፡፡ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ከኮምቦልቻ በ23 ኪ/ሜትር ርቀት ላይ ወደምትገኘው ደሴ ከተማ ጉዞ ተጀመረ፡፡ ደሴ ከተማ ደረስን፡፡ ተማሪዎች ከዚህ በፊት ስለማያውቁት መምህራኖቻቸው በ40 ደቂቃ ውስጥ ዞር ዞር ብለው ጎብኝተው እንዲመለሱ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ተማሪዎችም ትዕዛዝ መቀበላቸውን በጭብጨባ ገለጹ፡፡ የደሴን ከተማ በወፍ በረር ቅኝት 45 ደቂቃ ጎብኝተን ጨረስን፡፡ በ45 ደቂቃ ደሴን ያህል ከተማ እንዴት አይነት ጉብኝት ነው እንደምትሉኝ እገምታለሁ፡፡ በደሴ ከተማ የሚያምሩ ህንፃዎች፣ ፎቆች ተግንብተዋል፡፡ አብሮኝ ያለውን የሥራ ባልደራባየን እንዴት ነው ደሴ የተቀየረች ይመስልሃል? ብየ ጠየቁት፡፡ ‹‹አዎ እያየሃት እንዴታ በጣም ተለውጣለች›› አለኝ፡፡ ሰዓቱ ስላነሰን በቆይታችን ሳንደሰት ወደ መኪናችን እየሮጥን ሄድን ፡፡ ሰዓት ስላሳለፍን ሁሉም ገብተው እየጠበቁን ነበር፡፡ ይቅርታ ጠይቀን ገባን፡፡ ከደሴ ከተማ በ30 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ወደምትገኘው ሃይቅ ከተማ ጉዞችንን አደረግን፡፡ ከከተማዋ ደረስን፡፡ ሐይቅ ከተማ ወጣ ገባ የበዛባት ከተማ ነች፡፡ እንደዚህ አይነት ቦታ ላይ የተፈጥሮ ሐይቅ ማግኘት እጅግ ያስደንቃል፡፡ የሐይቅ ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ከሐይቁ በስተሰሜን በኩል አረንጓዴ ሆኖ ይታያል፡፡ ይህ ቤተክርስቲያን የተመሰረተው ንጉስ ድልነዓድ በነገሱ በሰባተኛው ዓመት መንግስት ከጳጳሱ ከአባ ሰላማ ጋር ወደዚች ደሴት እንደመጡና ቦታውን ሲያዩት እጅግ ስለወደዱት ቤተክርስቲያን ይሰራባት ብለው በማሰብ በዚያ ቦታ መሰረት ድንጋይ አስቀምጠው በ862 ዓ.ም ማሳነፃቸውንና ንጉስ ድልነዓድ በደሴቷና በቤተክርስቲያኑ እጅግ ተደስተው እንደነበር የቤተክርስቲያኗ ታሪክ ያስረዳል፡፡ እኛም ደሴቱን፣ የቤተክርስቲያኑን ከሐይቁ ጋር ግርማ ሞገስ እያየን ተደሰትን፡፡ ምን ይህ ብቻ በሐይቁ ዙሪያ የቤተክርስቲያኑ አባቶች ያለሙትን የሙዝ፣ የፓፓያ፣ የማንጎ እና ሌሎች አትክልቶች ለቤትክርስቲያኑ ልዩ ውበት ሰጥቶታል፡፡ ልማቱን እያደነቅን ወደ አጥር ግቢው ገባን፡፡ በግቢው ውስጥ ትንሽ እንደሄድን አንድ አባት ‹‹ኑ ልጆቸ ቤተመዘክሩን ላስጎብኛችሁ›› አሉን፡፡ ሁላችንም በፈግታ እሽታችን አሳይተን ተከተልናቸው፡፡ ቤተመዘክሩ ውስጥ የጥንት መሪዎች አጽም፣ በወቅቱ ሲጠቀሙባቸው የነበሩ የቤት ቁሳቁሶች፣ ታሪካዊ መጽሐፍት እና ሌሎችንም ከጎበኘን በኋላ አመስግነን ከቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ወጣን፡፡ ከቤተክርስቲያኑ በቅርብ እርቀት ወደሚገኘው ሎጂ ሄድን፡፡ ቀኑ ዕለተ ሰንበት ስለነበር በሎጁ ውስጥ ለመዝናናት የመጡ ብዙ ናቸው፡፡ ሎጁ ዘና ያደርጋል፡፡ አስተናጋጆቹ ወከባ ይታይባቸዋል፡፡ ትንሽ ደቂቃ ተቀመጥን እስካሁን አስተናጋጅ አጠገባችን አልመጣም፡፡ በጣም ስራ በዝቶባቸው እንደሆነ እያየን ስለሆነ አልፈረድንባቸውም፡፡ ወደ ቤተክርሲቲያኑ ጉብኝት ያልሄደ ከመካከላችን አንድ ተማሪ አገኘን፡፡ እንሂድ እንጂ አለን ፈጠን ብሎ፡፡ ጉዞ ማዕከል የነበረ አንድ ተማሪ ‹‹ምሳ ሳንበላ?›› አለ፡፡ ‹‹ኧረ ባክህ ተው! የተማሪ አይደለም በጣም ውድ ነው ሜኖውን ላሳይህ›› አለው፡፡ እንዲህ እያወሩ እያለ በአጠገቤ አንድ አስተናጋጅ ሲያልፍ እባክህ ሜኖ (የምግብና የመጠጥ ዝርዝር ዋጋ) አምጣልኝ አልኩት፡፡ አመጣልኝ እጀን በአፌ ያዝኩት እውነትም ለተማሪ የሚመጥን አይደለም፡፡ ኧረ ጎበዝ ተነሱ እንሂድ ይህ ለኛ አይሆንም አልኳቸው፡፡ የወቅቱን የንሮ ውድነት ታውቁታላችሁ፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ ተመሪነት፡፡ ለምን ብሎ የጠየቀኝ የለም፡፡ ወደ መሐል ከተማ ሄደን እንደ አቅማችን ምሳችን በላን፡፡ ከቀኑ 10፡30 ላይ የሚኪናችን ክላክስ ተሰማን፤ በፍጥነት ወደ መኪናችን ሄድን፡፡ የሐይቅ ከተማን ለቀን ወጥተን ከሐይቅ ከተማ በዘጠና ኪ.ሜትር ርቀት ወደ ምትገኘው

ወልድያ ከተማ ለመድረስ ጉዞ ተጀመረ፡፡

ወደ ገጽ 13 ዞሯል

**ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን**

የባለፈው ወር እትም ገፅ 16 ላይ ያለው ፎቶ የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ጥናት ተቋም የ2ኛ እና 3ኛ ዓመት ተማሪዎች ኤሊኖ በተከሰተባቸው ደቡብና ሰሜን ወሎ አካባቢዎች ላይ ምልከታ ሲያካሂዱ የሚያሳይ ምስል ነው፡፡ የዝግጅት ክፍሉ ለተፈጠረው ስህተት ውድ አንባቢዎቻችንን ይቅርታ እንጠይቃለን!

# “ነፃ አውጪው” ማን ነው?

## ቅኝ ገዢ፣ ነፃ አውጪ መሆን ይቻለዋልን?

ጀማል ሙሀመድ ሀይሌ (ዶ/ር)
ከጋዜጠኝነትና ስነተግባቦት ትምህርት ክፍል
jemalmohammed99@gmail.com

የመቐለ ከተማን ቁልቁል አፍጥጦ ከሚያያት ከሂል ቶፕ ሆቴል እራት እየበላን ነው፡፡ ጋባዣችን መቐለ ዩኒቨርሲቲ ሲሆን ተጋባዦቹ ለስራ ጉብኝት የሄድን የተወሰኑ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ነን፡፡ ከ18 አመት በታች ያሉ “ህፃናት” እንዳይጠጡት እየተባለ የሚጠጣው ቢራ እዚህም-እዚያም መከፈትና መታደል ሲጀምር በሳህን የያዝኩትን ምግብ ቶሎ-ቶሎ ጎረስ-ጎረስ አድርጌ ወጣሁ፡፡ በሀይማኖቴ ክልክል ነው፤ ሽታው ደግሞ ራስ ምታት ነው የሚለቅብኝ፡፡

ከውጭ ያለው ነፋሻ አየር ተቀበለኝ፤ ትንሽ ቀዝቃዛነት ቢኖረውም ደስ ይላል - የተደበረን አእምሮ የሚያፍታታ አይነት ነው፡፡ ከታች የመቐለ ከተማ ጥርት ባለ ሰማይ ላይ እንደ ወጣች ሙሉ ጨረቃ በኤሌክትሪክ መብራቷ ፏ ብላ ትንቀለቀላለች፡፡ ከዚያ ኮረብታማ ቦታ ላይ ከተሰራ ሆቴል ደጅ ላይ ለቆመ ሰው መቐለ ልትሸሽግ የምትችለው ነገር ያለ አይመስልም - የከተማዋ ዳርቻ ከምስራቅ እስከ ምእራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ቁልጭ ብሎ ይታያል…

ልቤ የመቐለ ከተማን ከማድነቅ መለስ አለ… ከደቂቃ በፊት ከእራት ቦታው በወሬ-ወሬ አንዱ ባልደረባችን “ ‘ነፃ አውጪ’ ተብሏል” በማለት ወደ ነገረን ጉዳይ ሀሳቤ ተመለሰ፤ ማብሰልሰል ያዝኩ… “ማን ነው ነፃ አውጪው?” የነገሩ መገለባበጥ እየገረመኝ አሁንም ራሴን እጠይቃለሁ፤ “ነፃ አውጪው ማን ነው?”…

### ባሕር ዳርና መለያዎቿ

ባህር ዳር ከተማ የምትታወቅበት በርካታ መለያዎች አሏት፡፡ የጣና ሀይቅና ደሴቶቹ፣ የደንገል ተክሏ (papyrus)፣ ዘንባባዎቿ፣ ከቅርብ-ርቀት ያለው የአባይ ፏፏቴ… ለአብነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡ ከአመት በፊት የከተሞች ቀን እዚህ ባህር ዳር ከተማ ውስጥ በተከበረበት ወቅት፣ የከተማው አስተዳደር የራሱን ስራዎች ለትእይንት ይዞ ለቀረበበት ቦታ መግቢያ በር አድርጎ ያሰራው ጎጆ ቤት የሚያክል አገልግል ነበር፡፡ አስተዋዋቂው፣ “ባህር ዳርን ‘በምን እንግለፃት’ ብለን ስናስብ፣ አገልግልን ጥሩ መገለጫ ሆኖ አገኘነው” በማለት ሲናገር መስማቴን አስታውሳለሁ፡፡ ስለሆነም ከጣና ሀይቅ ከሚገኘው የደንገል ተክል ከተሰፋ (ከተሰራ) በኋላ በከብት ቆዳ የሚለበጠው አገልግል ሌላው የባሕር ዳራችን መለያ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል ማለት ነው፡፡

እርግጥ ነው ይህ የከተማዋ አንድ መለያ የሆነው ወይም ለመሆን እየተቃረበ ያለው አገልግል፣ ከብዙዎቹ የባህር ዳር ከተማ ነዋሪዎች ቤት ውስጥ በጌጥነት ከግድግዳ ላይ ተሰቅሎ ወይም ከብፌ ላይ ጉብ ብሎ ባይገኝም በእንግድነት ወደ ባህር ዳር የሚመጡ ብዙዎቹ ሰዎች - አበሻውም፣ ፈረንጁም - ለማስታወሻ እየገዙት እንደሚሄዱ ይታወቃል፡፡ እናም የባህር ዳር አገልግል እግሩ ረጅም ነው - ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምስራቅ እስከ ምእራብ ኢትዮጵያ፤ ከአውሮፓ እስከ አሜሪካ፣ ከአፍሪካ እስከ ኤሺያ ተጉዟል፤ በመጓዝ ላይም ነው፡፡

ከአገልግልምርት ጋር ፉክክር በመግጠም፣ በመላ ኢትዮጵያ ለመሰራጨት ቆርጦ የተነሳ የመሰለ ምርት፣ አሁን-አሁን የመፈክር ባንዲራውን በተለያዩ ቦታዎች በማውለብለብ ላይ ይገኛል፡፡ እስካሁን ድረስ በብዙ የአማራ ክልል ከተሞች የመፈክር ባንዲራውን ሰቅሏል፡፡ በክልሉ ዋና-ዋና ከተሞች ማለትም በጎንደር፣ በደ/ታቦር፣ በወልድያ፣ በደሴ፣ በኮምቦልቻ፣ በደ/ማርቆስና በእንጅባራ የምርቱን የመፈክር ባንዲራ ማውለብለብ ከጀመረ አመታትን አስቆጥሯል፡፡ ከእነዚህ ትላልቅ ከተሞች ባሻገር ጥቂት በማይባሉ

> በባህር ዳር ከተማ ያሉ የጫት መሸጫና የመቃሚያ ቤቶች ቁጥርም - ልክ እንደ “ጃምቦ ሀውሶቹ” ሁሉ - እንደ አሸን መፍላታቸው ለማንም የተሰወረ አይደለም፡፡

አንዳንድ የወረዳ ከተሞች በተለይም ዋና-ዋና ከተሞቹን የሚያገናኙ አውራ ጎዳናዎች በሚያልፉባቸው ከተሞች ውስጥ የምርቱን የመፈክር ባንዲራ ማውለብለብ ከጀመረም ሰነባብቷል፡፡ ይህ “ድንቅዬ” ምርት ከአማራ ክልልም አልፎ በኦሮሚያ፣ በአዲስ አበባና በትግራይ ክልል አንዳንድ ከተሞች (ለምሳሌ አክሱም፣ ሽሬ፣ ወዘተ.) የመፈክር ባንዲራውን ሰቅሏል፡፡ እኔ እንዳለኝ መረጃ ከሆነ፣ እስካሁን የመፈክር ባንዲራውን ማውለብለብ ያልቻለው ላሊበላ ከተማ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ተደብቆ መገኘት ግን ይችላል፤ ስለሚችልም ምርቱ ላሊበላ ከተማም ይገኛል፡፡ በሰሜን ምእራብ እስከ መተማ፣ ሁመራ፣ ሽህዲ… ዘምቶ ባንዲራውን ሰቅሏል፡፡ ይህ “ድንቅዬ” ምርት ከሱዳን ክልል ውስጥ ከሚገኘውና የድንበር ግብይት ከሚካሄድበት ጋላባት (ቃላባት) ከተባለው ስፍራም ደርሷል፤ ባጭሩ ሱዳን ገብቷል፡፡

አንዱ አስገራሚ ነገር የዚህን ምርት የመፈክር ባንዲራ ሰቅሎ ለማውለብለብም ሆነ ምርቱን ለመሸጥና ለማከፋፈል የሚያጋጥም የቢሮክራሲ ውጣ ውረድና የመልካም አስተዳደር ችግር የሌለ መሆኑ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ቸርቻሪዎች በተለይም ከሌላ የሱቅ እቃ ጋር ደርበው የሚሸጡት “ቫት” ይቅርና የግብር ጣጣ የለባቸውም፤ የንግድ ፈቃድ የማውጣትም ሆነ በጥቃቅንና አነስተኛ ወይም አንድ ለአምስት የመደራጀት ግዴታ የለባቸውም፡፡ “በሱቃችሁ መያዝ የምትችሉት አንድ አይነት እቃ ብቻ ነው፤ ጫማ ከሆነ ጫማ ብቻ፣ ልብስ ከሆነ ልብስ ብቻ፤ ካልሆነ ሁለት የንግድ ፈቃድ አውጡ” የሚለው የንግድ ደንብም ይህን “ድንቅዬ” ምርት የሚሸጡትን አይመለከትም፡፡ ከብዙ የንግድ ህግ “ጣጣዎች” ነፃ የወጣ “ድንቅዬ” ምርት!

አንድ ግለሰብ ይህን ምርት በመሸጥ ተግባር መሰማራት ከፈለገ የሚጠበቅበት ምንድነው? ወደ አንድ ኮምፒውተር ቤት ሄዶ መፈክሩን ማፃፍ ብቻ! በማርከር ወይም በእስኪርቢቶ ደመቅ አድርጎ እራሱ ሊፅፈውም ይችላል፤ ፅሁፉ ትንሽ ቢወለጋገድም - ብቻ ይነበብ እንጂ - ችግር የለም፡፡ ከዚያ ከሱቁ በር፣ መስኮት ወይም ግድግዳ ላይ ይለጥፈዋል፡፡ ከዚያ የመፈክሩ ባንዲራ መውለብለብ ጀመረ ማለት ነው፡፡ ምን እያለ? “የባህር ዳር ጫት” አለ፡፡

### “የባህር ዳር ጫት”

በአማራ ክልል የተለያዩ ከተሞች ብቻ ሳይሆን ባንዳንድ የአጎራባች ክልል ከተሞች ጭምር በየቦታው ስሙ ተፅፎ በመነበብ ባህር ዳር ከተማን የሚወዳደር ሌላ ከተማ ያለ አይመስለኝም፡፡ የጫቱ የስርጭት ስፋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሆኑ የሚሸፍናቸውና ስሙን የሚያውለበልብባቸው ከተሞችና ክልሎች ቁጥር በፍጥነት እየጨመረ እንደሚሄድ መገመት አያዳግትም፡፡ ዞሮ-ዞሮ ግን አንዳንድ ሰዎች ወይም አገሮች የተለየ ነገር ሲኖራቸው እንደሚያደርጉት፣ ባህር ዳራችን “ከሌሎች የአገሪቱ ከተሞች በተለየ ሁኔታ ስሜ በብዙ ከተሞች ተፅፎ ስለሚገኝ በጊነስ መፅሀፍ ስሜ ይስፈርልኝ” የሚል አፍ ሊኖራት አይችልም - እያሰራጨች ያለው የሚያደነዝዝ እፅ ነውና፡፡ ይቅርታ የጫትን ባህሪ በወጉ አልገለፅኩትም… ካነቃቃ፣ ካመረቀነና ካሰከረ በኋላ የሚያፈዝ፣ የሚያደነዝዝ እፅ፡፡

በዚያ የመቐለ የእራት ምሽት አንዱ ባልደረባችን ስለመፈክር ሰቃዩ ምርት በመቐለ ከተማ መገኘት አለመገኘት ይጠይቃል - የዩኒቨርሲቲውን አንድ ምክትል ፕሬዝዳንት፡፡ ባልደረባችን ምናልባት በቆየንበት አንድ ቀን ውስጥ “የባህር ዳር ጫት አለ” የሚለውን መፈክር ስላላየ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክትል ፕሬዝዳንቱ እያሳሳቀ፣ “እናንተ ሳትረሱን እየላካችሁልን እንዴት እዚህ ይጠፋል?” በማለት መኖሩን አረጋገጠልን፡፡ ባልደረባችንም፣ “ ‘ነፃ አውጪ’ ተብሏል” በማለት ለባህር ዳር ጫት ቅፅል ስም እንደ ወጣለት “አበሰረን”፡፡ እናም ይሄውላችሁ የባህር ዳር ጫት ነው “ነፃ አውጭ” በሚል ቅፅል ስም የሚንቆላጰሰው ወይም የሚሽቃበጠው፡፡

የባህር ዳር ጫት፣ ባህር ዳር ከተማ ውስጥ የሚሸጥ ከሆነ ደግሞ የመፈክሩ ቃል ለየት ይላል - “የባታ ጫት አለ”፣ “የወራሚት ጫት አለ”፣ “የዘንዘልማ ጫት መሸጫ”፣ “የጎርደማ ጫት መሸጫ”… ነገሩ ስልቻ-ቀልቀሎ ነው - እነዚህ ቃላት “የነፃ አውጪው” ሌላ መጠሪያ ናቸውና፡፡

ጫት ከሚልኩ ሰዎች ባገኘሁት መረጃ መሰረት በአሁኑ ሰአት በየቀኑ ጫት ብቻ የጫኑ ሁለት FSR (ISUZU) የጭነት መኪናዎች ከባህር ዳር ወደ ወልድያና ደሴ ይላካሉ፤ ወደ አዲስ አበባ ደግሞ የዚህ እጥፍ፣ ማለትም አራት FSR የጭነት መኪናዎች በየቀኑ ይላካሉ፡፡ አንዱ FSR መኪና ከ15 እስከ 20 ኩንታል ጫት ይይዛል፡፡ ከምሽቱ ሶስት ሰአት አካባቢ ከዚህ ይነሳሉ፤ ከንጋቱ 11-12 ሰአት አዲስ አበባ ይገባሉ፡፡ መኪናዎቹ ወደ አዲስ አበባም ሆነ ወደ ደሴ ሲሄዱ በመስመራቸው ላይ ላሉ ከተሞች “ድርሻቸውን” እየሰጡ ነው የሚሄዱት - ከመዳረሻዎቻቸው አንፃር አነስተኛ ቢሆንም፡፡ በአመት በአማካይ ሀያ አምስት ሺህ ኩንታል ጫት ከባህር ዳር ወደ አዲስ አበባ ይላካል፡፡ የባህር ዳር አምራችነቷ ብቻ ሳይሆን የአዲስ አበባም ሆዳምነቷ አይደንቅም - ይህን ሁሉ የጫት ተራራ ያለ ይሉኝታ ስታመነዥገው? የጤፉና የማሩ አገር ጎጃም ወደ ጫት አገርነት እየተቀየረ ወይስ ሁለቱንም “ጎን-ለጎን እሰራዋለሁ” በማለት በድፍረት እየገባበት ያለ ንግድ ይሆን?

እዚህ ላይ “የባህር ዳር ጫት ለምን “ነፃ አውጪ” ተባለ? እንዴትስ “ነፃ አውጪ” ሊባል ቻለ? ማን ነው ነፃ አውጪ ያለው? ማንንስ ነው ነፃ የሚያወጣው?” የሚሉት ጥያቄዎች መነሳትና መልስ ማግኘት አለባቸው፡፡

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# እንግዳችን

## “በእኔ አመለካከት በአንድ ተቋም ወይም መሥሪያ ቤት ተቀጥሮ መሥራት ማለት አገርንና ራስን መጥቀም ማለት ነው፡፡”

አቶ በለጠ ተክሌ

የዛሬ ወር እንግዳችን በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ጋሼ የሚል ከበሬታን ያተረፉ በዩኒቨርሲቲው ለበርካታ አመታት ጡረታ ከወጡ በኃላም እያገለገሉ የሚገኙ በዩኒቨርሲቲው አመራር፣ በመምህራን፣ በሰራተኞችና በተማሪዎች ከፍተኛ ከበሬታን ያገኙ አንጋፋ ሠራተኛ ናቸው፡፡ የህይወትና የስራ ተሞክሯቸውን አስመልክቶ ከናይል ጋዜጣ ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡ ቃለ መጠይቁን እነሆ፡፡ መልካም ንባብ!

**ናይል፡-** በመጀመሪያ ለቃለ መጠይቃችን ፈቃደኛ ስለሆኑ በናይል ጋዜጣ እናመሰግናለን፡፡

**አቶ በለጠ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡



**ናይል፡- ስምዎትን፣ የትውልድ ቦታና የልጅነት አስተዳደገዎን ቢገልጹልን?**

**አቶ በለጠ፡-** ጤና ይስጥልኝ ስሜ በለጠ ተክሌ ካብትህ ይመር እባላለሁ፡፡ የትውልድ ቦታ§ በቀድሞው አጠራር በሸዋ ጠቅላይ ግዛት በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ በወራና ባሶ ወረዳ ታላቅ አምባ ገሊላ ማርያም ቀበሌ በ1942 ዓ.ም ከገበሬ ቤተሰብ ተወለድሁ፡፡ በገጠር እድገቴ እንደማንኛውም የገጠር ልጅ ከብት በመጠበቅና ማንኛውንም የእርሻ ሥራ በመሥራት ቤተሰቦቼን እያገለገልሁ ለተወሰነ ጊዜ በገጠር ቆይቻለሁ፡፡ በገጠር በቆዩሁበት ዘመን ለቀጣይ ሕይወቴ ጠቃሚ የሆኑ መልካም የሥነ ምግባር እሴቶችን ከወላጆቼ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ እና ከሃይማኖት ተቋማት መማር ችያለሁ፡፡

**ናይል፡- የትምህርት ቤት ህይዎትዎን አጠር አድርገው ቢገልጹልን?**

**አቶ በለጠ፡-** ድሮ ድሮ እኔ በተወለድኩበትና በአደግሁበት ዘመን የአካባቢው ማህበረሰብ ለትምህርት የሚሰጠው ዋጋ አነስተኛ ነበር፡፡ ት/ቤት ተከፍቶ ገበሬው ልጁን ወደ ት/ቤት የሚያስገባው በአጥቢያ ዳኛ እየተገደደ ነበር፡፡ ታዲያ እኔም በአጋጣሚ በራሴ ከፍተኛ ጥረትና በወላጆቼ የተለሳለሰ ፈቃዳኝነት ጕሼ ባዶ ት/ቤት ገብቼ ከ1-4ኛ ክፍል፣ ደብረብርሃን ከተማ አፄ ዘርያዕቆብ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ከ5-6ኛ ክፍል፣ ኃይለማርያም ማሞ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ከ7-12ኛ ክፍል በመማር ትምህርቴን ጨርሻለሁ፡፡ በቀጣይ በአምቦ እርሻ ኮሌጅ በዲፕሎማ በ1962 ተመርቄ በደብረማርቆስ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለ4 ዓመት በመምህርነት ሠርቻለሁ፡፡ ከዚያም ትምህርቴን የማሻሻል ፍላጐት ስለነበረኝ ከባህርዳር መምህራን ኮሌጅ በፔዳጐጂካል ሣይንስ ሜጀር በጂኦግራፊ ማይነር በ1979 ዓ.ም በመጀመሪያ ድግሪ ተመርቄአለሁ፡፡

**ናይል፡- ስለ ትዳር ህይወትዎ እና ቤተሰበዎ ያጫውቱን?**

**አቶ በለጠ፡-** በ1973 ዓ.ም ከባለቤቴ ጋር በመግባባትና በመፈቃቀር ትዳር መሥርተን ሁለት ልጆች ወልደን በሥርዓት አሳድገንና አስተምረን እራሳቸውን እንዲችሉና እንዲያስተዳድሩ አድርገናል፡፡ ከባለቤቴ ጋር ለ32 ዓመት በሰላምና በፍቅር ኖረናል፡፡ ኑሮአችንን ለማሻሻል ጥረት አድርገናል፡፡ ሆኖም ባለቤቴ ከ3 ዓመት በፊት ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቷ ሁኔታው የማይረሣ የሕይወት ጠባሳ ጥሎብኝ አልፏል፡፡

**ናይል፡- ወደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መቼ ተቀላቀሉ? እንዴትስ ተቀላቀሉ?**

**አቶ በለጠ፡-** በ1967 ዓ.ም በባሕርዳር መምህራን ኮሌጅ /Academy of pedagogy/ ሥር ይተዳደር የነበረው የአንደኛ ደረጃ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም /TTI/ ሲከፈት ከደብረማርቆስ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ወደ ባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅ በዝውውር መጥቻለሁ፡፡ በዚህም በባሕር ዳር 1ኛ ደረጃ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም / TTI / 10 ዓመት እንዲሁም በባሕርዳር መምህራን ኮሌጃ / Academy of pedagogy/የጐልማሶች ት/ክፍል 12 ዓመት በጠቅላላው ለ22 ዓመት በመምህርነት ሙያ ሠርቻለሁ፡፡ ከማስተማር ሥራ በተጨማሪ ለ1 ዓመት የባሕር ዳር መምህራን ማሠጠኛ ተቋም /TTI/ ዳይሬክተር በመሆን፣ የባሕርዳር መምህራን ኮሌጅ የጐልማሶች ት/ክፍል ተጠሪ በመሆን ለ4 ዓመት በኃላፊነት አገልግያለሁ፡፡

**ናይል፡- በዩኒቨርሲቲው በመምህርነት እና በአስተዳደር ሰራተኛነት እንዳገለገሉ ይታወቃል፣ እስቲ ስለዚህ ጉዳይ ያጫውቱን? ያለውስ ልዩነት ምን ይመስላል?**

**አቶ በለጠ፡-** በባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅ /Academy of pedagogy/ ቆይታዬ ከመደበኛ የማስተማር ሥራ በተጨማሪ የገቢ ማመንጫ እንዲሆኑ በተቋቋሙ የወተት ከብቶች እርባታ፣ የንብ እርባታ፣ የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ የልማት ዘርፎች ኃላፊና ተቆጣጣሪ በመሆን ለብዙ ዓመታት አገልግያለሁ፡፡ በ1989 ዓ.ም የጐልማሶች ት/ክፍል  ከተዘጋ በኃላ በተለይ በ1992 ዓ.ም የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ምሥረታን ተከትሎ የዋናው ግቢ የገቢዎች ማመንጫ ኃላፊ ሆኜ እንድሠራ ተመድቤ ለ6 ዓመታት ሠርቻለሁ፡፡ ከዚያም በ1998 ዓ.ም ዩኒቨርስቲው የርቀት ትምህርት ሲያቋቁም የርቀት ትምህርት የፈተና ክፍል ዳይሬክተር ሆኜ እንድሠራ ተመድቤ ክፍሉን በመምራት ለ10 ዓመት አገልግያለሁ፡፡ ወደ ባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅን /Academy of pedagogy/ ተዛውሬ ከመጣሁበት ጊዜ ጀምሮ በአካዳሚካዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ለረጅም ጊዜ ሠርቻለሁ፡፡ በሁለቱም የሥራ ዘርፎች በመስራቴ ጠቃሚ የሥራ ልምድ አግቻለሁ፡፡ በሁለቱም አቅጣጫ መሥራቴ የነበረኝ ዕውቀትና ክሕሎት እንዲሻሻል ረድቶኛል፡፡ በሁለቱም የሥራ ዘርፎች ለምሠራው ሥራ ያለኝ ፍላጐትና ተነሳሽነት ተመሳሳይ ቢሆንም በአብላጫነት የማስተማር ሙያን እወዳለሁ፡፡

**ናይል፡- በዩኒቨርሲቲው የርቀትና ተከታታይ ት/ጽ/ቤት ከምስረታው ጀምሮ እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ በጽ/ቤቱ ሥራ የታዩ ስኬቶችና ተግዳሮቶች ቢያካፍሉን?**

**አቶ በለጠ፡-** የባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ ርቀት ትምህርት የተቋቋመው በ1998 ዓ.ም ነው፡፡ ፕሮግራሙ ሲመሰረት ከመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች ቀደምት ፋናወጊ ነው፡፡ ፕሮግራሙ ከተመሠረተ 10 ዓመት አስቆጥሯል፡፡ በዚህም በመማር ማስተማር ሂደቱ በቂ ልምድ አዳብሯል፡፡ ልምዱንም ለሌሎች ዩኒቨርስቲዎች በማካፈል ላይ ይገኛል፡፡ በየሴማስተሩ የተማሪዎች ምዝገባ ብዛት ሳይዋዥቅ

⇨

# እንግዳችን ...

በዘላቂነት በተለያዩ የትምህርት ክፍሎች በርካታ ተማሪዎች ይመዘገባሉ:: ፕሮግራሙ ከተቋቋመበት ዓላማ አኳያ በርካታ ዜጐች ከሥራቸውና ከመኖሪያ አካባቢያቸው ሳይለዩ መማር ችለዋል:: በፕሮግራሙ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ከፍተኛ ነው:: የፕሮግራሙ ተደራሽነት በየዓመቱ እየተሻሻለ ነው:: በዚህም እስከ 2007 የትምህርት ዘመን መጨረሻ ድረስ ከ20,000 በላይ ተማሪዎች በመጀመሪያ ድግሪ ተመርቀዋል:: ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው በአገር አቀፍ ደረጃ የተማረ የሰው ኃይል ከማፍራት አኳያ የርቀት ትምህርት ፕሮግራም አጋዥነት ጉልህ ሚና እንዳለው አስመስክሯል:: ስለሆነም ፕሮግራሙ የታለመለትን ግብ መቷል ማለት ይቻላል:: በአጠቃላይ በተደረገው የፕሮግራሙ እንቅስቃሴ አጥጋቢ ውጤት ቢመዘገብም በቱቶሪያል ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ ማነስ፣ የሞጁል ሕትመት መዘግየት፣ የፈተና ውጤት መጥፋትና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሰው ኃይል አለማሟላት ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው::

**ናይል:- ወደፊት በጽ/ቤቱ ሲሰሩ የታሰቡ ሥራዎችን ቢገልፁልን? ወይም አሁን ካሉበት የተሻለ ለማድረግ ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ በለጠ:-** የርቀትና ተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የርቀት ትምህርት የተጀመረበትን 10ኛ ዓመቱን ሲምፒዚየም በማዘጋጀት ጥር 10/2008 ዓ.ም አክብሯል:: በጽ/ቤቱ በኩል የ10 ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ቀርቧል:: በቀረበው ሪፖርት በ10 ዓመቱ የሥራ እንቅስቃሴ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጐኖች በሲምፖዚየሙ ተሳታፊዎች ውይይት ተደርጐ ወደፊት በመማር ማስተማር ሂደትና በተማሪዎች አገልግሎት አሰጣጥ የተሻለ ሥራ እንዲሠራ ስምምነት ላይ ተደርሷል :: በዚህም የሞጅል ክለሳ እንዲደረግ፣ በE-learning የሚሰጡ ትምህርቶች በ2ኛው ሴሚስተር እንዲጀመሩ፣ የተማሪዎችን አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተም የSIMS አሠራር ተጠናክሮ መምህራን የተማሪዎች የፈተና ውጤት በSIMS አስገብተው ተማሪዎችም የፈተና ውጤት በየአካባቢያቸው የሚገኝ የኢንተርኔት አገልግሎትን በመጠቀም የፈተና ውጤት እንዲያዩ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ፣ የጽ/ቤቱና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሠራተኞች ከመደበኛ የሥራ ቀናት በተጨማሪ ቅዳሜ ጠዋት በመግባት ለተማሪዎች የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጥ የመግባባት ሥራ ተሰርቷል::

**ናይል:- ከዩኒቨርሲቲው በጡረታ ከተገለሉ በኋላ ባለዎት የሥራ ተነሳሽነት በዩኒቨርሲቲው በድጋሚ በመቀጠር እስካሁን እያገለገሉ ይገኛሉ:: እስቲ ስለዚህ አጠቃላይ ያለዎትን ተሞክሮ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ያስተምራል የሚሉትን ቢያካፍሉን?**

**አቶ በለጠ:-** በእኔ አመለካከት በአንድ ተቋም ወይም መሥሪያ ቤት ተቀጥሮ መሥራት ማለት አገርንና ራስን መጥቀም ማለት ነው:: ማንኛውም መሥሪያ ቤት ለሠራተኛ መተዳደሪያ ሥራ ይሰጣል ሠራተኛውም መተዳደሪያ ሥራ ለሰጠውም ተቋም ተገቢውን አገልግሎት መስጠት ይጠበቅበታል:: በአንፃሩም ተቋሙ ሠራተኛው ለሚሰጠው ተገቢ አገልግሎት የደመወዝ ዕድገት፣ የትምህርትና ሥልጠና ዕድል ማመቻቸት ይኖርበታል:: በዚህ ዓይነት ግንኙነት ተቋሙም ሆነ ሠራተኛው የየድርሻቸውን ኃላፊነት በተገቢው መንገድ ከተወጡ የተቋሙ ዕድገት ይፋጠናል:: ሠራተኛውም ተጠቃሚ ይሆናል:: ይህ የመደጋገፍ ጉድኝት ግንኙነት ለመግለፅ አንድ የማኔጅሜንት መርህ / Principle/ ብጠቅስ ደስ ይለኛል:: "What is good for the Institution it is also good for the Individual and vice versa" :: በዚህ መርህ መሠረት በሥራ ዓለም ቆይታዬ መጀመሪያ ለምሠራበት ተቋም ክብር እሰጣለሁ:: የተሰጠኝን ሁሉ ያለምንም መለሳለስ በተገቢው መንገድ እፈፅማለሁ:: ለእኔ መኖር ተገቢ ሥራ መሥራት ወሳኝ መሆኑ ይገባኛል:: በመሆኑም የመሥራትና የሥራ ተነሳሽነቴ ጡረታ ከመውጣቴ በፊት ሆነ በኃላ ያው ነው:: በዚህም ዩኒቨርስቲው ጡረታ ከወጣሁ በኃላ በኮንትራት እየተቀጠርኩ እንድሠራ ዕድል ስለሰጠኝ በሙሉ ፍላጐት ተነሳሽነት በመሥራት ላይ እገኛለሁ::

**ናይል:- እርስዎ በመንግስት መስሪያ ቤት የሚፈፀምን የሙስና እና የመልካም አስተዳደር ጥሰት በጣም እንደሚቃወሙ ይታወቃል:: ጥሩ ዜጋ ከማፍራት አንፃር ለትውልዱ ምን ይመክራሉ?**

**አቶ በለጠ:-** በተፈጥሮዬ ከምጠላቸው መጥፎ የሰዎች ሰብዕና መካከል ሌብነት፣ እምነት ማጉደል እና የሰዎችን መብት ማጓደል ዋንኞቹ ናቸው:: እኔ በልጅነት እድገቴ ከ1-12ኛ ክፍል ድረስ የግብረ-ገብ ትምህርት በመማሬ ከገጠር ወላጆቼ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከእምነት ተቋማት የቀሰምኩት ጠቃሚ ማሕበራዊ እሴቶች ሰብዕናዬን ገርቶታል ብዬ አምናለሁ:: ይህን ተሞክሮ የሕይወቴ መመሪያ በማድረግ በሥራ ዓለም ቆይታዬ ሰዎች አፈንጋጭ የሆኑ ድርጊቶችን ሲያራምዱ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለማረምና ለመከላከል አቅም ፈጥሮልኛል:: ስለዚህ ከእኔ ተሞክሮ እንደምገምተው ጥሩ ዜጋ ለማፍራት ቤተሰብ፣ የእምነት ተቋማት ማህበረሰብና የትምህርት ተቋማት ወሳኝ ሚና መጫወት ይገባቸዋል:: ለአንድ ግለሰብ ሆነ ማህበረሰብ ዕድገትም ይሁን ውድቀት መንሥኤው ቤተሰብ ነው:: በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ ጥሩ ዜጋ ለማፍራት ወላጆች ልጆቻቸውን ገና ከሕፃንነታቸው ጀምሮ መልካም ማህበራዊ እሴቶችን ማለት ለሰው ልጅ ክብር መስጠት፣ ቤተሰብንና ታላላቆችን ማክበር፣ ከሌሎች ጋር አብሮ መሥራት፣ የሰውን መብት መጠበቅ፣ ሕግን ማክበር፣ አገርን መውደድ፣ በአጠቃላይ 12ቱን የሥነ ምግባር መርሆችን እንዲያውቁ በተግባር የሚታዩ ምሳሌዎችን በማንሣትና ውይይት በማድረግ ሥነ-ሥርዓት ባለው መንገድ ኮትኩተውና አንፀው ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል:: በሁለተኛ ደረጃ ጥሩ ዜጋ ለማፍራት በትምህርት ተቋማት ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ በየደረጃው የሚሰጠው የሥነ ዜጋ ትምህርት አግባብነቱና ይዘቱ በየጊዜው እየተጠና ተጠናክሮ መሰጠት ይኖርበታል::

**ናይል:- በዩኒቨርሲቲው ለረጅም ዓመታት አገልግዋል:: በዚህ የሥራ አለም ቆይታዎ አሳዛኝም ሆነ አስደሳች ገጠመኝ ይኖረዎታል እስቲ ስለገጠመኝዎት ያጫውቱን?**

**አቶ በለጠ:-** የሰው ልጅ ስሜት /emotion/ ሁልጊዜ በየደቂቃው፣ በየሳዓቱና፣ በየቀኑ ተለዋዋጭ ነው:: አንዴ ደስ ይለናል ሌላ ጊዜ ይከፋናል:: ሕይወት ማለት ይኸ ነው:: የመጀመሪያ ልጄ ሲወለድ ባለቤቴ ሆስፒታል ገብታ ምጥ በርትቶባት ሥቃይዋ ለ10 ሰዓት ያህል ዘልቆ ነበር:: በማዋለጃ ክፍል መስኮት ውጭ ሆኜ ስቃይዋን አዳምጥ ነበር:: በመጨረሻም በዕለተ ሐሙስ ቀን ልክ ከቀኑ 10 ሰዓት ሲሆን የልጄን ድምፅ ሰማሁ:: ወዲያውኑ ነርሷ በመስኮት ብቅ ብላ "ደስ ይበልህ ወንድ ልጅ አግኝተሀል" አለችኝ:: ከመቅጽበት በሕይወቴ የመጨረሻውን ደስታ ተጓናፀፍኩ:: ሲቃ ይዞኝ እንባዬ ዱብ ዱብ አለ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለእኔ 10 ሰዓት ማምለኪያ ነው:: ዘወትር ቀንም ሆነ ሌሊት 10 ሰዓት ሲሆን የመንፈስ ደስታ ይሰማኛል::

**ናይል:- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 አፍሪካ ከሚገኙ 10 ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ለመሆን ራዕይ ማስቀመጡ ይታወቃል:: ዩኒቨርሲቲው ይህን ራዕዮን ለማሳካት ምን መሥራት አለበት ብለው ያስባሉ?**

**አቶ በለጠ:-** ባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ አሁን በደረሰበት ደረጃ ግዙፍ ተቋም ነው:: በዓይነትም ሆነ በጥራት በቂ የሰው ሀብት አለው:: በዕድገት ሂደቱ ዩኒቨርስቲው ባደረገው እንቅስቃሴ በርካታ ስኬቶች ተመዝግበዋል:: የትምህርት ፕሮግራም ዓይነቶች በርካታ ናቸው፣ የድህረ ምረቃ ፕሮግራም እየተጠናከረ መጥቷል፣ የምርምር ሥራዎች በየዓመቱ በመጨመር ላይ ይገኛል:: እነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴዎች ለዩኒቨርስቲው ራዕይ መሳካት ግብዓቶች ናቸው:: የዩኒቨርስቲውን ራዕይ ለማሳካት ተቋሙና ማህበረሰቡ በቁርጠኝነት የየድርሻቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ይጠበቅባቸዋል:: ዩኒቨርሲቲው የአመራሩን ሚና በማጠናከር ወደ ራዕዩ መሳካት የሚያደርሱ ተያያዥ ዕቅዶችን ነድፎ ተግባራዊነታቸውን በመከታተል፣ ለሥራና ምርምር አስፈላጊና ተገቢ ግብዓቶችን በማሟላት፣ ከውጭና ከአገር ውስጥ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርምር ሥራ ልምድ በመቅሰም፣ የሠራተኛውን የሥራ ባሕልና አመለካከት በማዳበር የበኩሉን ድርሻ መውጣት ይገባዋል:: በአንፃሩም የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ በራዕዩ ዙሪያ የያገባኛል ስሜትን ሰንቆ ራዕዩ ይሣካል የሚል አስተሳሰብ አንግቦ የዩኒቨርሲቲው ራዕይ መሳካት ይመለከተኛል ባይ ሆኖ በነጠላና በጋራ አድራጊና ፈጣሪ በመሆን ድርሻውን በቁርጠኝነት ከተወጣ ራዕዩ የማይሳካበት ምክንያት አይኖርም::

**ናይል:- በመጨረሻ ማመስገን የሚፈልጉት አካል ካለዎት እድሉን እንስጥዎ?**

**አቶ በለጠ:-** የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህራን ኮሌጅ /Academy of pedagogy/ ተከፍቶ በ1966 ዓ.ም ሥራ የጀመረው በ21 ኢትዩጵያውያን በ11 የውጭ አገር ዜጐች መምህራን በ20 የአስተዳደር ሠራተኞችና በ94 ተማሪዎች ሲሆን በረጅም የታሪክ ሂደት ባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅ አሁን ዩኒቨርሲቲው በደረሰበት ደረጃ በዓመት 53343 ተማሪዎች የሚያስተናግድ እና 5834 መምህራንና ሠራተኞችን የሚያስተዳድር ግዙፍ ዩኒቨርሲቲ ሆኖ ማደጉ የሚያበረታታ የታሪክ አጋጣሚ ነው:: በመሆኑም በፈጣን የዕድገት ሩጫ ቅብብሎሽ ሂደት ተቋሙን አሸናፊ ለማድረግ ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱትን በአጠቃላይ የዩኒቨርሲቲውን ኃላፊዎችና ሠራተኞ ላደረጉት ጥረት በጣም አመሰግናለሁ:: በመጨረሻም ለማመስገን ዕድሉ ስለተሰጠኝ አመሰግናለሁ::

ናይል:- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን!

**አቶ በለጠ:- እኔም አመሰግናለሁ!**

# የጉዞ ማስታወሻ

በአምሳሉ ጥላሁን

መኪናዎች ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ፊታቸውን አዙረው ጉዞ ጀመሩ:: የባቲን መንገድ ስንያያዝ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ስለነበር አካባቢው በጣም ይሞቃል:: ሁላችንም ለመንገዱ አዲስ እንደመሆናችን ሙቀቱን ለመቋቋም እየሞከርን የአካባቢውን መልካ ምድር ጋራው ሸንተረሩን በግርምት መመልከት ጀመርን:: ከኮምቦልቻ ከተማ በግምት ወደ አስር ኪ.ሜትር እንደወጣን የምንሄድበት መንገድ አዲስ የአስፋልት ስራ ላይ ስለነበር ተለዋጭ መንገዱ መንገዱ ለጉዞ እጅግ አስቀያሚ ነበር:: ተጓዥ ተማሪዎች ላይ የዝምታ ድባብ ይታያል:: ይህ መንገድ እንዴት ያደርገን ይሆን የምንወጣው እያሉ ለህይወታቸው የሚያስቡ ይመስላሉ:: ለምን ብትሉኝ የኔም ጭንቀት ስለነበር ነው:: ይህን የሚያስረግጥ ክስተት በአንዳንድ ሴት ተማሪዎች ጉንጭ ላይ እንባ መታየቱ ነው:: ‹‹ምነው ለምን ታለቅሻለሽ?›› ብዬ አንዷን ጠየኳት:: ፈራ ተባ እያለች ‹‹አይ ደህና ነኝ፣ መንገዱ በጣም ያስፈራል፣ የምንመለስ አልመሰለኝ አለችኝ›› ውስጤ ላይ ፍርሃት ቢያረብብም ፈገግ አልኩኝ:: ‹‹አንተ ትስቃለህ አይታይህም? ነው ያንተ ነፍስ የተለየች ነች?›› አለችኝ ቁጣ አይሉት ንዴት በተቀላቀለበት አንደበት:: ‹‹አይዟችሁ ይህ ምንም ማለት አይደለም በሰላም እንደርሳለን:: ሹፌራችን ደግሞ አስተማማኝ ነው:: ምንም ስጋት አይገባችሁ እሺ እህቶች›› አልኳቸው ሌሎችንም በአይኔ እየቃኘሁ:: አንገታቸውን በመወዝወዝ እሽታቸውን ገለጹልኝ:: ነገሩስ እውነታቸውን ነው ሁላችንም እግዚአብሔር ይጠብቀን እንጂ አልኩኝ በውስጤ::

ከኮምቦልቻ በ42 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው የባቲ ከተማ በጣም ሩቅ ሆና ታየች:: ከሁለት ሰዓት ጉዞ በኋላ የባቲን ከተማ አገኘናት:: ሁሉም መጮህ እና ማጨብጨብ ጀመረ:: ከኛ በፊት መምህራንን ይዛ የመጣችውን መኪና መፈለግ ጀመርን፤ ልናገኛት አልቻልንም:: የት እንደሄዱ ግራ ተጋብተን ፍለጋዉን ቀጠልን:: በግምት 400 ሜትር ርቀት አካባቢ አገኘናቸው:: የምሳ ሰዓት አልፎ ስለነበር ምሳ በ30 ደቂቃ ውስጥ በቶሎ በልተን እንድንመለስ ከሹፌራችን ትዕዛዝ ተሰጠን:: የተሰጠንን ትዕዛዝ ለመተግበር ሁላችንም በአራቱ አቅጣጫ በመበታተን ምግብ ቤት ፍለጋ ጀመርን:: መቼም የራበው ሰው ምግብ የሚያማርጥበት ጊዜ የለም:: ምግብ የሚጣፍጠው ሲርብ ነው ያለው ማን ነበር? የተገኘውን ሁሉ በልተን ከሁለት ተማሪዎች በስተቀር ሁላችንም በሰዓቱ ደረስን::

የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ጥናት ተቋም መምህር በሆኑት ዶ/ር አብርሐም መብራት አማካኝነት በኢሊኖ ምክንያት በአስር ዓመት ውስጥ አንድ ጊዜ በሚፈጠረው የአየር መዛባት የሚከሰተው የተፈጥሮ ድርቅ አደጋ ሀገራችን ላይ እያስከተለ ያለውን ጉዳት ለመመልከት ከባቲ ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ የምትገኘውን የቢራ ቀበሌ በባቲ ወረዳ እንደምንጎበኝ ተነገረን:: ጉብኝቱን የምናካሂደው የግብርና ጽ/ቤት የእንስሳትና የአሳ ሐብት የሥራ ሂደት አስተባባሪ በሆኑት በአቶ ሰይድ መሐመድ መሪነት እንደሆነም ተገልጾልን ከአቶ ሰይድ ጋር ወደ መኪናችን ገባን:: ሁላችንም የመጣንበት መንገድ በጣም መጥፎ ስለነበር ከዚህ የባሰ ይመጣ ይሆን የሚል ጥያቄ ማንሳታችን አልቀረም:: አቶ ሰይድም እርስ በርሳችን ስናወራ ሰምቶ ነበር እና ሳቅ እያለ መንገዱ አስቸጋሪ እንዳልሆነ ገለጸልን:: እኔም ጠጋ ብዬ የድርቁን ሁኔታ እንዴት ነው? ብዬ ለአቶ ሰይድ ጥያቄ አቀረብኩ:: አቶ ሰይድም በባቲ ወረዳ ውስጥ ካሉ 28 ቀበሌዎች ውስጥ 13ቱ በድርቁ በጣም ጉዳት እንዳደረሰባቸውና ሌሎች ቀበሌዎች ላይ መካከለኛ ጉዳት እንዳስከተለባቸው ገለጸልኝ:: ጉዳቱ በጣም የበረታባቸው ቀበሌዎች ላይ መንግስት የተለያዩ እርዳታዎች እየሰጠ እንደሆነ እና በጣም

> አመጋገባችንን ያየ ሰው እነዚህ ሰዎች ከምግብ ተለይተው ነው እንዴ የሰነበቱት ያሰኛል:: ያሻቸውን ይበሉ እንዴት እንደራበን የምናውቀው እኛ ነን::

አስቸጋሪ እየሆነ የመጣውን የውሃ ችግር ለመቅረፍ አራት የከርሰ ምድር ውሃ በመቆፈር ውሃ ወጥቶ አገልግሎት እየሰጠ እንደሆነም ጠቆመኝ::

መኪናችን ቢራ ቀበሌ ስለደረሰ ጥያቄዬን በማቆም ከመኪናችን ወረድን:: ከወረድንበት ቦታ በ200 ሜትር ርቀት ላይ በደርግ መንግስት የተገነባውን የቢራ ግድብ የሁላችንም ቀልብ ሳበው:: ይህ ግድብ የተገነባው በአካባቢው መስኖ ልማት ለማካሄድ ታስቦ በአሁኑ ወቅት ለመስኖ አገልግሎት እየዋለ አይደለም:: ይሁን እንጂ ግድቡ በድርቁ ምክንያት ብዙዎቹ የባቲ አካባቢ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ለራሳቸውም ሆነ ለእንስሳቸው ውሃ በጣም ውድ በሆነበት ዘመን እንደፈለጉ እንዲጠቀሙ እና ከግድቡ ግርጌ የሚገኙትም ቢሆን በግድቡ ምክንያት የሚመነጨውን የምንጭ ውሃ በቀላሉ እንዲያገኙ ረድቷቸዋል:: እኛም ግድቡ በዚያ በርሐ የሚሰጠውን ዘርፈ ብዙ አገልግሎት በማድነቅ በባቲ ወረዳ ውስጥ በከፍተኛ ድርቅ ጉዳት ውስጥ የሚገኙትን ቀበሌዎች በሙሉ መጎብኘት የሚያስችለን ጊዜ ስላልነበረን ቢራ ቀበሌ ብቻ በማየት ጉብኝታችንን ደመደምን::

አዳራችን ኮምቦልቻ ከተማ ስለሆነ ጉዞችንን ወደ ኮምቦልቻ ማድረግ ግድ ሆነብንና ወደ መኪናችን እየተሯሯጥን ገባን:: ሹፌሩም በፍጥነት የእኛን መግባትና የጊዜው መምሸት ስለተረዳ በፍጥነት መኪናውን ማስነሳት ጀመረ:: የሁላችንም ሃሳብ ስንመጣ በጣም አስቸግሮን ወደነበረው መንገድ ሆነ:: በመካከላችን ፀጥታ ሰፍኗል:: መምሸቱ በጣም ቢያሳስበንም ሙቀቱ ወደ ቀዝቃዛ አየር ስለተቀየረ ጥሩ ሆኖልናል:: የመኪናችን ሹፌር አቶ ሙሉጌታ በጣም የተረጋጋ እና በአፍላ ጉልበት ላይ ያለ ወጣት ነው:: ‹‹ስጋት አይግባችሁ፣ እንደርሳለን አሁን እኮ መንገዱም ቢሆን እንደ ቅድሙ አዲስ አይሆንብኝም አሁኑኑ ነው ከተፍ የምንለው›› ሲለኝ በጣም ደስ አለኝ:: ትንሽ እንደቆየሁ ግን ሃሳብ ገባኝ ቶሎ ለመድረስ ሹፌራችን የሚያደርገው ፍጥነት የተሞላበት አነዳድ ደስ አላለኝም:: ኸረ ችግር የለም ቀስ ብለን እንገባለን ለምን አልልውም በሚል ጥያቄ እኔው ለኔው ማንሳትና መጣል ጀመርሁ:: ከራሴ ጋር ክርክር ውስጥ እያለሁ የሥራ ባልደረባዬ የሆነው አቶ ታምራት ምነው ዝምታ አበዛህ ብሎ በእጁ ነካ ነካ ሲያደርገኝ ከክርክሬ ተመለስሁ:: ሹፌሩ ስጋት አይግባችሁ ይበል እንጂ እኛ ከስጋት አላመለጥንም በማለት ለራሴ ነገርኩትና ‹‹ስማ ታሜ ሹፌሩን ቀስ ብለን እንደርሳለን በለው›› አልኩት:: እሱም ‹‹እሺ ብሎ ሙሌ ሙሌ…›› አለው ሹፌሩም ‹አቤት ታሜ› አለ:: ‹‹አይዞህ!! ቀስ ብለህ ንዳ እንደርሳለን›› አለው:: ሹፌሩም ‹‹መርሃባ ታሜ›› አለው:: እኔም ከሃሳብ ነፃ ሆንኩኝ:: ከስራ ባልደረባዬ ታምራት ጋር በምሽቱ በጣም የሚያስደስተውን ጋራ እየተመለከትን፣ በመቅረጸ ምስል ወድምጻችን ምስልም እያስቀረን በጣም ሩቅ የነበረውን መንገድ ሳናውቀው አጠናቀን ኮምቦልቻ ከተማ ከምሽቱ 1:30 ላይ ደረስን:: የኮምቦልቻ ከተማን በምሽቱ ተራራ ላይ ሆነን ስንመለከታት የወረዳ ከተማ ሳትሆን የክልል ከተማ ትመስላለች፤ የምትማርክ ከተማ ናት:: ከዛሬ አራት ዓመት በፊት ኮምቦልቻን የሚውቅ ሰው አሁን ያለችበትን የዕድገት ጎዳና ማየት ራሱ በጣም ደስታን ይፈጥርለታል::

የኮምቦልቻ ከተማ በአማራ ክልል ከሚገኙ ከተሞች ብቸኛዋ የኢንዱስትሪ ከተማ እና የደረቅ ወደብ መገኛ ከተማ ነች:: እኔም እንደማገኛውም ኢትዮጵያዊ የከተማዋን ዕድገት በጣም ስላስደሰተኝ ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር ባጃጅ በኩንትራት ያዝንና ከተማዋን በከፊል ከጎበኘን በኋላ የባጃጁ ሹፌሩን ‹‹እንዴት ነው ኮምቦልቻ ላይ የአልጋ ችግር ይኖር ይሆን?» ብዬ ጠየኩት:: ‹‹ከሁለት ሰዓት በኋላ ላታገኙ ትችላላችሁ›› ስላለኝ አልጋ ወደ አለበት አካባቢ ውሰደን ብለነው ጉዞውን ቀጠለ:: የት እንደሚወስደን ባናውቅም ባለባጃጁን በማመን እሱ አልጋ በቀላሉ ይገኝበታ ወደ አለው ቦታ ወሰደን:: አልጋ ግን አላገኘንም:: በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን የወሎ እንግዳ አክባሪነትና እስካሁን ያልተሸረሸረ ባህላቸውን እንደጠበቁ መቆየትና ለምንጠይቃቸው ጥያቄ ምላሽ ትህትናቸውና አክብሮታቸውን ስመለከት ሳላደንቅ ማለፍ አልወደድኩም:: እኛም የወሎ ገራገርነት በአፈታሪክ ብቻ ሳይሆን በተግባር እያየን ተገረምን:: ከሁለት ሶስት ጥየቃ በኋላ የምናርፍበት ሆቴል አገኘን:: እንግዲህ የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል ይላል የሀገሬ ሰው:: እራት ለመብላት አልጋችን አካባቢ ወደ ሚገኘው ምግብ ቤት አመራን፤ ቁመቷ መካከለኛ፣ አይኖቿ ጎላ ጎላ ያሉ፣ እርጋታዋ የተለየ ውበት የሰጧት ኮረዳ ለጆሮ ምቹ በሆነ ድምጽ ‹‹ምን ልታዘዛችሁ?›› አለችን:: እኛም በጣም ርቦን ስለነበር በቀጥታ ወደ ምግቡ ትዕዛዝ ገባን:: ትዕዛዝ ተቀብላ ከሄደች በኋላ ተመልሳ መጣችና ትዕዛዙ ምን ምን ነበር? ብላ ጠየቀችን እኛም ራባችን ማስታገስ ስለነበረብን ክርክር ከማንሳት የጠየቀችንን ጥያቄ ወደ መመለሱ ቀጠልን:: በጣም ደስ የሚለው የታዘዘው ምግብ በአስር ደቂቃ ውስጥ መጣልን:: አመጋገባችንን ያየ ሰው እነዚህ ሰዎች ከምግብ ተለይተው ነው እንዴ የሰነበቱት ያሰኛል:: ያሻቸውን ይበሉ እንዴት እንደራበን የምናውቀው እኛ ነን:: ትዕዛዛችን የተቀበለችው አስተናጋጅ የራሃብ አጎራረሳችን ያሳሰባት ይመስል በፍጥነት የውሃ ብርጭቆዎችን ከፊት ለፊታችን ላይ ቁጭ ቁጭ በማድረግ ውሃ ቀዳችልን:: ከመሃከላችን አንዱ እናመሰግናለን ቆንጆ አላት:: ልብን ቀጥ በሚያደርግ ፈገግታ አይኖቿን እያንከራተተች ምንም ሳትመልስለት ሄደች:: ተመግበን ጨረስን:: ምስጋናውን ያቀረበላት ጓደኛችን በረጅሙ ተነፈሰ:: ምነው? ብዬ ጠየቁት:: ‹‹ኧረ ምንም›› አለኝ:: እሺ ብዬ ውሃየን እያወራረድኩ ‹‹አንድ ነገር ይቀረናል ከመተኛታችን በፊት›› አለኝ:: ‹‹ምንድን ነው እሱ?›› አልኩት:: ‹‹አንድ አንድ ቢራ እንጠጣ›› አለኝ:: ተስማማን:: ጓደኛዬም ፊታ ዘና አለና አስተናጋጇን ጠራት:: ‹‹አቤት ምን ልታዘዝ አለች?›› ትህትና በተሞላ አንደበት:: «ፊትሽ ላይ ጥሩ ነገር አይታይብሽም ምነው?» አላት:: «አቦ መርቅኜ ነው›› አለችው:: የልጅቷ ግልጽነት ከማህበረሰቡ የተገኘ በመሆኑ ያስደስታል:: በአመላለሷ ጓደኞቼ በሳቅ ፈካ አሉ:: አንድ አንድ ቢራ ከተጎነጨን በኋላ ሁሉም ይብቃን ሲሉ አንዱ ጓደኛዬ ‹‹ለእኔ ሁለተኛ አምጭልኝ ደካማ ሁሉ›› አለ:: ‹‹ወንድሜ ደክሞናል መተኛት እንፈልጋለን›› ሌሎች ተከላከሉ:: የእኔን ፍላጎት ከመድገሙ ነበርባ የሚጋራኝ በማግኘቴ ደስ አለኝ:: ሁለተኛው ቢራችን ጠጥተን ሁላችንም በአንድነት ወደ መኝታ ቤታችን አመራን:: በሰላም እደሩ ተባብለን ወደ መኝታ ክፍላችን ገባን:: በሰላም ያዋለኝን አምላክ አመስግኜ ተኛሁ:: ከንጋቱ 11:30 ላይ ነቃሁ:: ከአንሶላዬ ሳልወጣ ‹‹ሌሊቱን በሰላም ያሳደርከኝ በሰላም አውለኝ ተመስገን›› አልኩኝ::

በማግስቱ እሁድ ስለነበር ጓደኞችን ከእንቅልፋቸው ቀስቅሼ ወደ ቤተክርስቲያን አመራን:: ወሩ ታህሳስ በመሆኑ በጣም ይቀዘቅዛል::

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# “ነፃ አውጪው” ማን ነው?…

ከገጽ 7 የዞረ

“ነፃ አውጪ” ተብሎ የሚጠራ ወይም ራሱን የሚጠራ አካል ካለ ቢያንስ ሶስት ነገሮች መሟላት አለባቸው፡፡ አንድ ራሱ “ነፃ አውጪው” ወይም “ ‘ነፃ አውጪ’ ነኝ” ባዩ መኖር አለበት፤ ሁለት “ነፃ የሚወጣ” ወይም የተጨቆነ አካል መኖር አለበት፤ ሶስት የተጨቆነውን “ነፃ እንዳይወጣ” ያደረገው ወይም “ጨቋኝ” የሆነ አካል መኖር አለበት፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ “ነፃ አውጪ” ሊኖር አይችልም፡፡ ከዚህ አንፃር የባህር ዳር ጫት “ነፃ አውጪ ነው” ከተባለ፣ አንደኛ - ማንን ነው ነፃ የሚያወጣው? ሁለተኛ - ጨቋኙ ማን ነው? ሶስተኛ - የባህር ዳር ጫት ራሱ እንዴት ነፃ አውጪ ሊሆን ቻለ? የነፃ አውጪነትን ዘውድ የጫነለትስ ማን ነው?

የባህር ዳር ጫት የ“ነፃ አውጪነት” ርእይ (scope) ከቃሚዎቹ ውጭ ያሉትን ሰዎች እንደማይመለከት ግልፅ ነው ወይም አያከራክርም፡፡ “የለም፤ ‘ነፃ የሚያወጣው’ የማይቅሙትን ሰዎች ነው፡፡ ለምሳሌ የማይቅሙትን ጎልማሶች እንዲቅሙ፣ መቃም ያልጀመሩትን ወጣቶች እንዲቀማምሱ በማለማድ” ከተባለ ለባሕር ዳር ጫት የተሰጠው “ነፃ አውጪ” የሚል ስያሜ የቅኔም-ቅኔ (በስድ የሚነገር ቅኔ ካለ)፣ የሽሙጥም-ሽሙጥ ሆነ ማለት ነው፡፡ ይህ ሁኔታ እኔ ስያሜውን ከተረዳሁበት መንገድ ውጭ ነው፡፡ እናም ይህ ፅሁፍ የ”ነፃ አውጪውን” ጉዳይ በዚያ መንገድ አይተነትንም…

<u>“ነፃ አውጪ”</u>

ከባህር ዳር ከተማና በዙሪያው ካሉ የእርሻ ቦታዎች የሚመረተው የጫት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ፣ በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችንም ማክበሩ ጭምር የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡ በባህር ዳር ከተማ ያሉ የጫት መሸጫና የመቃሚያ ቤቶች ቁጥርም - ልክ እንደ “ጃምቦ ሀውሶቹ” ሁሉ - እንደ አሸን መፍላታቸው ለማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ በጥቂት አመታት ውስጥ የተፈለፈሉት የጀበና ቡና ቤቶች ቡና ለሚጠጡ ሰዎችና ለስራ አጦች ጥሩ አማራጮች የመሆናቸውን ያህል፣ የኢትዮጵያውያንን የቡና መጠጣት ባህል “ከጓዳ ወደ አደባባይ” በማውጣት ይበልጥ እንዲታወቅ ያደረጉትን ያህል፤ ብዙዎቹ ለጫት ቃሚዎች ተጨማሪ የመቃሚያ እልፍኝ በመሆን በማገልገል ላይ መሆናቸውም ግልፅ ነው፡፡ በቤታቸው፣ በሱቃቸውና በጫት መቃሚያ ቤት ከሚቅሙት የባህር ዳር ጫት ደንበኞች የተረፉትን እነሱ ያስተናግዳሉ፡፡ ከድርጅታቸው ውስጥ ጫት መቃምን የማይከለክሉ አንዳንድ ካፌዎችም አሉ፡፡ የፊልም ወይም የእግር ኳስ ጨዋታ ማሳያ አዳራሾችም ከዚሁ የሚደመሩ ናቸው፡፡ አሁን-አሁን ደግሞ ወደ አንዳንድ ሱቆችና ድርጅቶች በር ጠጋ ብሎ ከውጭ በኩል መቃም (የደጅ ቂምሀ) ብቅ-ብቅ እያለ ነው - የከተማው አስተዳደር “የጣና ፈርጥ” እያለ በሚያንቆላጵሳት ከተማ በባሕር ዳር፡፡ ቁጥራቸው ትንሽ ቢሆንም መኪና በተለይም ባጃጅ ይዘው ወደ ከተማዋ አንድ ዳርቻ ወጣ በማለት የሚቅሙም አሉ፡፡ እናስ - የባሕር ዳር ጫት “ነፃ አውጪነት” ከምኑ ላይ ነው? ነው ወይስ እነዚህ ሁሉ ቦታዎች የተጨቆኑትን ነፃ ለማውጣት ጫቱ ትግል የሚያካሄድባቸው የውጊያ ቀጠናዎች መሆናቸው ነው?

የቃሚዎቹን ማህበራዊ ደረጃ ስናይ ደግሞ በባህር ዳር ጫት “ያልተለከፈ” የህብረተሰብ ክፍል ማግኘት ይከብዳል፡፡ መምህሩ፣ ተማሪው፣ ነጋዴው፣ ባለሙያው፣ ሀላፊው፣ ምንዝሩ፣ ጋዜጠኛው፣ ፖለቲከኛው፣ ሾፌሩ፣ ሀኪሙ፣ የቀን ሰራተኛው፣ ሴተኛ አዳሪዋ፣ ጎዳና ተዳዳሪው… ከፆታ አንፃርም ልዩነት የለም - የሴቶች ተሳትፎ ጭምር የተረጋገጠበት ነው (የዚህስ “እኩልነት” ምነው በቀረባቸው?) ከእድሜ አንፃር ሲታይም ከህፃናት በስተቀር በሁሉም የእድሜ ክልል ያሉ ባህር ዳሬዎች ይሳተፉበታል፡፡ እናስ ማን ቀረ? (እብድን ማማት ለወሬ አይመችም እንጂ ከአእምሮ ህሙማንም በርካታ ተሳታፊዎች አሉት)፡፡

ባጭሩ ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል “ቀላል” የማይባሉ ንቁ የቂምሀ ተሳታፊዎች አሉት፡፡ የባህር ዳርን ጫት ለዚህ ያበቃው ምንድነው? የባህር ዳር ጫት እንደ ወጥ ቅመም በግራም እየተመዘነ ስለሚሸጥ፣ በሚቃመው መጠን ካልሆነ በስተቀር፣ በሀብታምና በድሀ መካከል ልዩነት አይፈጥርም፡፡ ለሁሉም ተደራሽ ነው፡፡ ለምሳሌ አዲስ አበባ ውስጥ ከባሕር ዳር ጫት በስተቀር ሌሎቹ የጫት አይነቶች በግራም አይሸጡም፡፡ የሚሸጡት የጫት ሻጩ ዛላዎቹን በእጁ በመጨበጥ ወይም ዘላዎቹን በእጁ በመመዘን ነው፡፡ ከዚያ ንቅንቅ የለም፡፡ ስለሆነም ከውድነቱ የተነሳ ሀብታሞች ብቻ የሚቅሙት የጫት አይነት አለ፡፡ የሀብታም፣ ሀብታም የሆኑት ሰዎች ብቻ የሚቅሙት የጫት አይነትም አለ፡፡ የባሕር ዳር ጫት ግን በዚህ አይታማም፡፡ ተደራሽነቱ ገደብ የለውም፡፡

ያም ሆነ ይህ የባህር ዳር ጫት “ነፃ አውጪ” ከተባለ፣ ከፍ ሲል የተጠቀሱት የህብረተሰብ ክፍሎች - ከአለቃ እስከ ምንዝር፣ ከተማሪ እስከ መምህር፣ ከሀብታም እስከ ድሀ፣ ከትልቅ እስከ ትንሽ - የባህር ዳርን ጫት ስለሚቅሙ “ነፃ የወጡ ናቸው” ማለት ነው? የባህር ዳር ጫት “ነፃ አውጪ” የተባለበት ሚስጥሩ ከቶ ምን ይሆን? አንድ ንኡስ ክፍለ ጦር ሊያደራጅ ይቅርና አንድ ምንሽር ወይም ክላሽ ሳይታጠቅ፣ አንድ ጥይት ሳይተኩስ ወይም ቢያንስ-ቢያንስ “በሰላማዊ መንገድ እታገላለሁ” የሚል አንድ ለፈስፈስ ያለ ፓርቲ እንኳን ማቋቋም ሳይችል፣ የባህር ዳር ጫት “ነፃ አውጪ” የመባሉ ሚስጥር ምንድነው?

ብዙ ጊዜ በወርቅ የሚመሰለውን ጊዜን ለመግደል ስለሚረዳ ይሆን “ነፃ አውጪ” ያሉት? በስራ ከመወጣጠር፣ በትምህርት ከመጨናነቅ “ነፃ ስለሚያወጣ” ይሆን “ነፃ አውጪ” ያሉት? በየቀኑ ለሚገኝ ምርቃና፣ ከዚያም ስካር፣ ከዚያም መደንዘዝ ገንዘብን ስለሚያስወጣ ይሆን “ነፃ አውጪ” ያሉት? ግለሰቦችን የሱስ እስረኛ የማድረግ ጥበብ “ስለተካነ” ይሆን “ነፃ አውጪ” ያሉት? የወጣትነትን ትኩስ ወኔ ስለሚያሟሽሽ፣ የወጣትነትን አፍላ የስራ ፍቅር ስለሚሰልብ ይሆን’ንዴ “ነፃ አውጪ” ያሉት? ከቁም የቅዠት ባህር ከቶ፣ ያልዘሩትን ስለሚያሳጭድ፣ ያልወቁትን ስለሚያሳፍስ ይሆን’ንዴ “ነፃ አውጪ” ያሉት? ከ“በርጫ” ወደ “ጨብሲ” (ከቂምሀ በኋላ አስካሪ መጠጥ መውሰደ) ከ“ጨብሲ” ወደ ሴት አዳሪ እንደ ከብት ስለሚነዳ ይሆን’ንዴ “ነፃ አውጪ” ያሉት? ያለ “በርጫ” ቀኑ የማይመሽ፣ ያለ “ጨብሲ” ሌሊቱ የማይነጋ ስለሚያስመስል ይሆን’ንዴ “ነፃ አውጪ” መባሉ? ወተት የመሰሉ ጥርሶችን ካርታሜን ያላመጡ እስከሚመስሉ ድረስ ስለሚያስውባቸው፣ የወጣቶችን ወዝ እንደ አልቀት መጥጦ ፊታቸውን ተነቅሎ እንደ ከረመ ጎመን ስለሚያስቆነጀው ይሆን “ነፃ አውጪ” መባሉ? አንዳንድ ነጋዴዎች ንግዳቸውን እንዲከስሩ፣ አንዳንድ የመንግስት ሰራተኞች ከስራ እንዲባረሩ፣ አንዳንድ ሰዎች ትዳራቸውን እንዲበትኑ ስላስቻለ ይሆን “ነፃ አውጪ” መባሉ? የህሊናን ሰላም ስለሚዘርፍ፣ የአእምሮን መስከን ስለሚሰርቅ፣ የስሜትን መረጋጋት ስለሚነጥቅ ይሆን “ነፃ አውጪ” መባሉ? ድንቄም ነፃ አውጪ!

**ይቀጥላል!**

## የፀረ ሙስና ቀን…

ከገጽ 5 የዞረ

ለመዘርጋት ረቂቅ ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን በቅርቡም ወደ ተግባር በመግባት ሁሉም እንደጥፋቱ የሚጠየቅበት አሰራር እንደሚኖር ተገልጿል፡፡ በተለይ የመልካም አስተዳደር በቅጥር እና ደረጃ እድገት አወጣጥ ላይ ችግር ፈጣሪ የሆኑ ኃላፊዎች፣ በተማሪዎች አገልግሎት የምግብ አቅርቦት እና በግዥና ንብረት አስተዳደር ጥራቱን ያልጠበቀና እቃ ማስገባትና የተጋነነ ዋጋ ግዥ ችግሮች ላይ መሰረት በማድረግ ማስረጃዎችን እየሰበሰበ ምርመራ በማካሄድ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለማድረግ ጽ/ቤቱ ከፍተኛ ሥራ እየሰራ እንደሚገኝ ታውቋል፡፡

## ቫይረሱ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ …

ከገጽ 4 የዞረ

አስማረ እንደገለፁት ኤች አይ ቪ/ኤድስ በ2007 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ የኢትዮጵያ የጤናና ስነ ሕዝብ ያወጣውን መረጃ መሰረት በማድረግ በሀገራችን ብሎም በክልላችን ያለበት ደረጃ በየአመቱ በኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያዙ ሰዎች ከ16 ሺ በላይ ሲሆን በበሽታው ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት ደግሞ 733 ሺ በላይ ናቸው፡፡ በበሽታው እየተጠቁ የሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍል አምራቹ ኃይል የሆነው ወጣት መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

በፓናል ውይይቱ ጥናታዊ ጽሁፍ የቀረበ ሲሆን ኤች አይ ቪ/ኤድስ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ያደረሰውን ጥፋትና አሁን ያለበት ደረጃ ተገልጿል፡፡ በሽታው ከታወቀበት ጊዜ እ.ኤ.አ 1981 ጀምሮ በአለም አቀፍ ደረጃ ተመርምረው ራሳቸውን ያወቁ 40 ሚሊዮን ሰዎች ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ 12 ሚሊዮኑ ህይወታቸውን ያጡ ሲሆን ቀሪዎቹ ደግሞ ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ ተገልጿል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል የተሰባሰቡ አምራች ኃይል የሚባሉት ተማሪዎችን ተቀብሎ የሚያስተምር እንደመሆኑ ተማሪዎቹ በበሽታው ሳይጠቁ ሀገራቸውን እንዲጠቅሙ ለማድረግ ዳይሬክቶሬቱ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር እየሰራ ይገኛል፡፡ አምራቹ ኃይል በበሽታው እንዳይጠቃ ለማድረግ ግንዛቤ ከማስጨበጥ ባሻገር ለተማሪዎች የህይወት ክህሎት ስልጠና በመስጠት እርስ በርስ የሚማሩበት መድረክ ተፈጥሮ የመከላከል ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በየአመቱ ስልጠናዎችን በማዘጋጀትና በመስጠት በተለይ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ተጋላጭነት አስተዋፅኦ አላቸው በተባሉ የአደንዛዥ እፆች ተጠቃሚዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ከዚህ የሚወጡበት እና ከወጡም በኋላ የህይወት ልምዳቸውን ለሌሎች ተማሪዎች እንዲያካፍሉ ለማድረግ ስልጠና ይሰጣል፡፡ በዚህ የሕይወት ክህሎት ሥልጠና በርካታ ተማሪዎች ከአደንዛዥ እፅና አልኮል ተጠቃሚነት ሕይወት እንዲወጡ ተደርጎ የሰላም ህይወት እንዲኖሩ መደረጉ በፓናል ውይቱ ላይ ተገልጿል፡፡

በተጨማሪም ዳይሬክቶሬቱ በራሪ ወረቀቶችን በማዘጋጀት ተማሪዎች የበሽታውን አስከፊነት እንዲያውቁት ከማድረግ በተጨማሪ የተለያዩ አስተማሪ የመዝናኛ መድረኮችን በማዘጋጀት ተማሪዎች ከመዝናኛ መድረኩ ጠቃሚ መልዕክቶችን እያገኙ ራሳቸውን እንዲጠብቁ ለማድረግ ሥራዎች

ተሰርተዋል፡፡

## ነግበኔ …

ከገጽ 14 የዞረ

“ይሄኔ እሷንም እንደዚህ ብለሃት ነበር፡፡ በፍጹም እንዳትከተለኝ!” እንደጠቀመጠ ጥላው ሄደች፡፡ በሩጋር ከመድረሷ በፊት ከኋላዋ ያዛት፡፡ በንዴት ዞራ “አፈቀርኩሽ ከማለትህ በፊት ፍቅሩ ልብህ ላይ መኖሩን አረጋግጥ፡፡ ምላስህ ከጭንቅላትህ አይቅደም!!” ብላው መንጭቃው ሄደች፡፡ በድጋሚ ሲይዛት በጥፊ አጩላው ሄደች፡፡ አልተከተላትም፡፡

የጠዋቱን ብርድ ለመርታት፣ ትኩስ ነገር ለመጠጣት፣ በዛውም ቁርስ ለመብላት፣ የገቡ ተስተናጋጆችን ሲያይ አፈረ፡፡ ሁሉም አፍጠውበታል፡፡ ሁሉም እንዲሰሙ እየጮኸ መናገር ጀመረ፡፡

“ውሻ ናት! ልክስክስ ውሻ!! ይቺ እስስት! ምንም የማትረባ ሸርሙ. . .”

ሄለን የኤልያስን ንግግር ከኋላዋ እየሰማች ሄደች፡፡ ነግበኔ ብላ ከሱ መለየቷ ተገቢ እንደሆነ ለራሷ እየነገረች ተጓዘች፡፡ ደብረብርሃን እየተሟሟቀች ነው፡፡ ሰው ይወጣል ይወርዳል፡፡ ህይወት ቀጥላለች፡፡

**ይቀጥላል!**

# ነግበኔ

በታምሩ ከፈለኝ (የሻረግ)

፪ኛ አመት የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል ተማሪ

www.facebook.Com /ደቀ ከፈለኝወ የሻረግ

ፀሃይ ከምስራቅ አድማስ ተንጠልጥላ አረጃጅም እግሮቿን ቁልቁል ዘርግታለች፡፡ የዘረጋችው እግሯ መጋረጃው በተገለጠው መስኮት ገብቶ ከአንሶላ አምልጦ የወጣው የኤልያስ እግር ላይ አርፏል፡፡ ኤልያስ ግን ለፀሃዩዋ እግር ቦታ አልሰጠም፡፡ የጦፈ እንቅልፉን ይለጥጣል፡፡ በርግጥ ወደ መኝታው የሄደው ከእኩለ ሌሊት በኋላ ነበር፡፡ እኩለ ሌሊት ድረስ ለፍቅረኛው ይመጥናል ብሎ ባሰበው መልኩ የተለያዩ ፅሁፎችን ሲፅፍ አመሸ፡፡ የፃፋቸውን ሲያነባቸው የፍቅሩን ፅናት መግለፅ የሚችሉ ስላልመሰለው ቀዶ ጣላቸው፡፡ እንቅልፍ እንቢ ስላለው ሲገናኙ የሚጋብዛትን ሙዚቃ ለመምርጥ ዲቪዲ ማጫወቻውን አብርቶ የርቀት መቆጣተሪያውን(Remot control) አነሳ፡፡ በርካታ የፍቅር ዘፈኖችን አዳመጠ፡፡ ከሁሉም ግን ልቡ ውስጥ የቀረው "የኔ ማር" የሚለው የአብዱ ኪያር ሙዚቃ ነበር፡፡ የኔ ማርን እያንጎራጎረ ወደ መኝታው ሄዶ ተኛ፡፡

የቱ ውበት ነው እንደአንቺ የተዋጣለት

የቱ አመል ነው ዕንከን ማይገኝለት

ልብን ወስዶ መንፈስ የሚገዛ

የሚያሸንፍ ቀን በቀን የሚበዛ

ይሄ ሁሉ መባረክና ማማር

ነው ምንጩ ንገሪኝ እስኪ የኔ ማር

የኔ ማር… የኔ ማር… የኔ ማር…የኔ ማር

ራስጌው ጠረንጴዛ ላይ ያስቀመጠው ተኝቀሳቃሽ ስልኩ ጮኸ፡፡ ኤልያስ ጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ስለነበር የስልኩን ጩኸት አልሰማም፡፡ በድጋሚ ጮኸ፤ ምላሽ የለም፡፡

*    *    *    *

ሄለን በለሊት ልበሷ አንሶላ ውስጥ እግሯን ዘርግታ ተቀምጣ የተነቀሳቃሽ ስልኳን ቁልፎች እየነካካች ወደ ጆሮዋ ትወስድና በብስጭት ከጆሮዋ ላይ ትመነጭቀዋለች፡፡ ንዴቷ ፊቷን ደም አስመስሎታል፡፡ ትላልቅ አይኖቿ ፈጠዋል፡፡ ፀጉሯ ተበታትኗል፡፡ ጡቶቿ ከሌሊት ልብሷ አፈንግጠዋል፡፡ ደረቷ ላይ የብር መስቀል በወፍራም ክር ተንጠልጥሏል፡፡ እንደዛ ሆና ሲመለከቷት ጣኦት ትመስላለች፡፡ የምትንቀሳቀስ፤ ህይወት ያላት ጣኦት፡፡

በድጋሚ ስልኳን አንስታ የተወሰኑ ቁልፎችን ነካክታ ወደ ጆሮዋ ወሰደችው፡፡ ብዙም ሳይቆይ በተንቀሳቃሽ ስልኳ ውስጥ የሾለከ ጎርናና ድምፅ ወደ ጆሮዋ ገባ፡፡ የኤልያስ ድምፅ ነበር፡፡

"እ…እ አ..ቤት"

"አልተነሳህም እንዴ"

"እ..ህ..ህ አረ ተነስቻለሁ"

"እና ስደውልልህ ለምንድነው የማታነሳው"

"እ… ደውለሽ ነበር?"

"እሺ አሁን በደንብ ንቃና አናግረኝ"

"ነቅቻለሁ እኮ…. እንዴት አደርሽልኝ" የኤልያስ ድምፅ እየተስተካከለ መጣ፡፡

"በሰላም ነው እስካሁን የተኛኸው?"

"ማታ በጣም አምሽቼ ነበር የተኛሁት፡፡"

"ዛሬ እንገናኝ"

"እሱማ ግድ ነው"

"አምስት ሰዓት ሚኪ ካፌ እንገናኝ"

"አይቻልም እሱ ቤት ጥሩ ነገር አያስታውሰኝም፡፡ ሌላ ቦታ እንገኛኝ፡፡"

ኤልያስ ሚኪ ካፌ መግባት እንደማይወድ ታውቃለች፡፡ ለምን ብላ ስትጠይቀው የበፊት ፍቅረኛዬን ያስታውሰኛል ይላታል፡፡ ለዚህም ሌላ ቦታ ይገናኛሉ፡፡ ግን ስለ ቀድሞ ፍቅረኛው ከማውራት ተቆጥቦ አያውቅም፡፡ ሁሌም "ያቺ እርኩስ ህይወት የምትባል ሴት እንዲህ ታደርግ ነበር…."

"ስሟን ቄስ ይጥራውና ህይወት እንዲህ ትለኝ ነበር…"

"ያቺ ሴይጣን ህይወት እዚህ ይዛኝ ትመጣ ነበር"

"ያቺ ሌባ. . . "

"ያቺ ሽር. . ." ይላል፡፡ ሄለን እንዲህ እያለ ሲናገር ደስ ስለማይላት በተደጋጋሚ ስለሷ እንዳያወራ ነግራዋለች፡፡ ደግሞ ላያወራ በስሟ ምሎላት ማላው ካፉ ሳይጠፋ በድጋሚ ስሟን ይጠራል፡፡ ህይወትን፡፡

ሄለን "የቀድሞ ፍቅረኛህ እንጂ ጠላትህ አይደለችም ብዙ ጥሩ ነገር አሳለፋችኋልና እባክህ ስሟን በክፉ አታንሳ" ብላ መከረችው፤ አልሰማም፡፡ አስመከረችው፤ አልሰማም፡፡ የሱ አንሶ ስልክ ቁጥሯን ለጓደኞቹ እየሰጠ አሰደባት፡፡ ሄለን ግን ትእግስቷ አልቋል፡፡

"እሺ ሜላት እንገናኝ"

"ጥሩ አሁን ስንት ስዓት ነው"

"ሁለት"

"በቃ እመጣለሁ እንዳታረፍጂ"

"ቻው"

"ቻው! ሁሌም አፈቅርሻለሁ"

ሄለን የተገናኙ ሰሞን እንደዚህ ሲላት ልቧ ኩራት ይሰማውና ትፍነከነክ ነበር፡፡ አሁን አሁን ግን ምንም አይሰማትም፡፡ ድንገት ቢጣሉ እሷንም እንደ ህይወት እወድሻለሁ ባለበት አፉ በስድብ እንደሚያጥረገርጋት አትጠራጠርም፡፡ ከመኝታዋ ተነስታ ቤቷን አስተካክላ ወደ ሜላት ካፌ ለመሄድ ልብሷን ቀየረች፡፡ ፀጉሯን አበጥራ ግራ ቀኝ ለቀቀችው፡፡ ረጅም ፀጉሯ ከቀጭን ሰውነቷ ጋር የውበት ንግስት አደረጋት፡፡ ሰዓቷን

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

ፈጣን መረጃ

## በ2008 ዓ.ም በውጭና በሀገር ውስጥ የተመሠረቱ ግንኙነቶች

| Established Partnership in 2008 E.C | |
|---|---|
| 1 | Szent Istavan University |
| 2 | Northwestern Polytechnic University |
| 3 | Dubai University |
| 4 | HZB Research Center (Helmohltz center Berlin) |
| 5 | UCS (Univesidadedecaxiasdosul) |
| 6 | Sudan University of Science and Technology |
| 7 | Veroniza State Technical University |
| 8 | Istanbul University |
| 9 | University of Basilicata |
| 10 | University Deglli Studi Roma Tre |
| 11 | Texas Tech University |
| 12 | Confucius Institute |
| 13 | Entrepreneurship Development Center (EDC) |
| 14 | Helen Doron Educational Group |
| 15 | Boku, University of Natural Resources and life sciences, Vienna |
| 16 | Emirates College for Science and Engineering |
| 17 | University of Gadarif |
| 18 | Adama Science and Technology University |
| 19 | The Nile project |
| 20 | University of Havana |
| 21 | University of De Pinar Del |
| 22 | Gambela University |

| BDU is a member of (Memebership) | |
|---|---|
| 1 | International Universities Association |
| 2 | The African Network of Scientific and Technological Institutions |
| 3 | Association of African Universities (on progress) |

# የጉዞ ማስታወሻ ...

ከገጽ 6 የዞረ

ከምሽቱ 12:30 ላይ ወልድያ ደረስን፡፡ ተማሪዎችም ወልድያ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ገብተው ማደር ስላለባቸው መኪናው ዋናውን መንገድ ለቆ በስተቀኝ በኩል ወደሚገኘው ወደ ወልድያ ዩኒቨርሲቲ በር ታጠፈ፡፡ በሩ ላይ እንደደረስን የዩኒቨርሲቲው የጥበቃ ሰራተኞች አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ ‹‹ምን እንርዳችሁ›› በማለት ተቀበሉን፡፡ አቀባበላቸው ደስ ይላል፡፡ ስርዓታቸውና ትህትናቸው ለሌሎች የዩኒቨርሲቲዎች የጥበቃ ሰራተኞች ምሳሌ የሚሆኑ ናቸው፡፡ መሽቶ ስለነበር ወደ ጉዳያችን ገባን፡፡ ለዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች አገልግሎት ኃላፊ ስልክ ደወለን ስልኩ ግን አይሠራም፡፡ ምን ይሻላል ተማሪዎች የግድ ማደሪያ ማግኘት አለባቸው፡፡ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት መደወል ግድ ሆነ፡፡ ስልክ ደወልኩ ‹‹ሀሎ ሀሎ›› አሉኝ ፕሬዚዳንቱ ነበሩ ‹‹ጤና ይስጥልኝ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ነው የምደውለው›› አልኳቸው፡፡ ‹‹እሺ ምን ልርዳህ›› አሉኝ፡፡ ይቅርታ ፕሮፌሰር ተማሪዎችን ይዘን ወደ ዩኒቨርሲቲያችሁ መጥተናል እና ለእነሱ የሚሆን ማደሪያ እንዲፈቀድልን እባክዎትን ፍቃድ ይስጡን ብዬ ነው፡፡ እሺ ችግር የለም አንድ አምስት ደቂቃ ጠብቁኝ የሚመለከታቸውን እልካለሁ አሉኝ፡፡ አምስት ደቂቃ ሳይሞላ የሚመለከተው አካል ተላከልን፡፡ እንዲህ ነው ቀልጣፋ የማህበረሰብ ቁርጠኛ አገልግሎት አልኩኝ፡፡

ተማሪዎችን አስገብተን የእኛን መኝታ ቤት ፍለጋ በባጃጅ ለመሄድ ተገደድን፡፡ መኪናችሁስ? እንዳትሉኝ ብቻ፡፡ ለተማሪዎች የተዛዘ ስለነበር ከዚያው ትተን መጣን፡፡ ልክ አንድ ሁለት እርምጃ እንደተራመድን አንድ ቲዎታ መኪና መንገድ ዳር ቆማለች፡፡ የሥራ ባልደረባዬ አቶ ታምራት ወደ መኪናዋ ጠጋ ብሎ ‹‹ወደ ከተማ ብትወስዱን?›› አላቸው፡፡ ከሾፌሩ አጠገብ የተቀመጠ አጠር ወፈር ብሎ ቦርጩ ገፋ ያለ እድሜው 45 ዓመት አካባቢ የሚገመት ሰውዬ መኪናው የመንግስት ስለነበር ‹‹ይህ መኪና እኮ የሁላችንም ነው ኑ ግቡ›› አለን፡፡ ‹‹እናመሰግናለን›› ብለን በደስታ ወደ ውስጥ ገባን፡፡ ሾፌሩ ወደ መሃል ከተማው እየገሰገሰ ነው፡፡ በአምሮዬ እዚች ሃገራችን ውስጥ የመንግስት ገንዘብ የግል የሚመስላቸው ባለስልጣኖችን አሰብኩና ከዚህ ሰውዬ ጋር አነፃፀርኳቸው፤ ምንም የማያውቁንን ሰዎች የመንግስት ገንዘብ የህዝብ ነው ብለው በማሰብ እንድንገለገል መፍቀዳቸው፤ በጣም ይገርማል፡፡ ከገብስ መሐል እንክርዳድ አይጠፋም እንደሚባለው አይነት ናቸው ማለት ነው፤ በዚህ ሃሳብ ውስጥ እንዳለሁ ጋቢና ላይ ያለው ሰውዬ ‹‹እንግዳ ትመስላላችሁ ከየት መጣታችሁ ነው?›› አለኝ፡፡ ‹‹አዎ እንግዳ ነን፡፡ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ›› አሉኳቸው፡፡ ‹‹ባሕር ዳር ከተማ በጣም ነው የምትመቸኝ፡፡ በክልል አመራርነት አገልግያለሁ፡፡ ከተማዋ አሁን በጣም ተለውጣለች›› አሉኝ፡፡ ‹‹አዎ በጣም እንጂ›› አልኳቸው በልበ ሙሉነት፡፡ ለምን እያዳላህ ነው እንዳትሉኝ በክልላችን ካሉት ከተሞች ውስጥ ማንም እንደማይወዳደራት በማሰብ ነው፡፡ ‹‹አዎ እውነት ነው›› አሉኝ፡፡ ሆቴሎች ወደሚገኙበት አካባቢ ስለደረስን አመስግነን ከመኪናቸው ወረድን፡፡ በአካባቢው ብዙ አልጋ ቤቶች ስላሉ ሳንቸገር ሆቴል በቀላሉ አገኘን፡፡ እራታችን ከዚያው ሆቴል ውስጥ ተመግበን ወደ መኝታ ክፍላችን ገባን፡፡ ያደርንበት አልጋ በጣም ፀጥታ የሰፈነበት ስለነበር ከእንቅልፌ የነቃሁት በጓደኞቸ ቅስቀሳ ነበር፡፡ ምን አለበት ዛሬን የእረፍት ቀን ቢያደርጉት እያልኩ ወደ እጅ መታጠቢያ ክፍል በመሄድ እጄንና ፊቴን ስታጠብ እንቅልፌ ለቀቀኝ፡፡ ሾፌራችን በሩ ላይ ተማሪዎችን ይዞ በክላክስ ጠራን፡፡ ልብሶቸን ይዤ ወጣሁ፤ ደግሞ ዛሬ የት ይሆን የምንሄደው? አልኩት ሾፌሩን፡፡ ‹‹ምነው እስካሁን? እንዴ የጥዋት ጉዞችን አስረፈድክብን እኮ›› አለኝ፡፡ በጣም ይቅርታ ደክሞኝ ስለነበር መሰለኝ፡፡ ‹‹አይዞህ በርታ በል እንጂ›› አለኝ ሳቅ እያለ፡፡ ጉዞ ተጀመረ ወልድያ ከተማ ወደ አስር ኪ.ሜትር ርቀት ከሄድን በኋላ ከመኪና እንድንወርድ ከመንገዳችን በስተቀኝ በኩል የተዘራውን ማሽላ ሰብል ተማሪዎች እንዲያዩትና ጥያቄ ወይም ማብራሪያ የሚያስፈልገው ነገር ካለ እንዲጠይቁ ዶ/ር አብርሃም ጋበዟቸው፡፡ ተማሪዎችም ወደ ማሽላው ማሳ አቀኑ፡፡ ማሽላው ፍሬ ሳያፈራ ገና በቅጠሉ እንደደረቀ አየን፡፡ ተማሪዎች እርስ በራሳቸው ‹‹በጣም የሚያሳዝን ነው ምንም አይነት ፍሬ አልያዘም!›› እያሉ ተገረሙ፡፡ መምህር አብርሃም ግን ከዚህ በፊት መጥተው አካባቢውን ስላዩት ‹‹ገና ምኑን አያችሁትና›› አሉ በሎሆሳስ ድምፅ፡፡ ተማሪዎችም ምንም አይነት አስተያየት ሳይሰጡ ወደ መኪናው አመሩ፡፡

ሁሉም ከገቡ በኋላ ዶ/ር አብርሐም መብራት ተማሪዎችን ‹‹ከዚህ በኋላ መኪናው ቀስ ብሎ ስለሚሄድ አካባቢውን በደንብ እያያችሁ ሂዱ›› አሉ፡፡ በመኪናው መስኮት በኩል ወደ ውጭ ማየት ጀመርኩ፡፡ አልፈው አልፈው ለምልመው የሚታዩት የጃትሮፋ እንዲሁም የግራር ዛፎች እየተመለከትሁ ጉዞችን ቀጠለ፡፡ ከዚህ በፊት በተለየዩ ሰብሎች ተሸፍና የሚታይ የነበረው የራያ ቆቦ መሬት እርቃኑን ይታየኝ ጀመር፡፡ ራያ መሬት የማኛ፣ ጤፍና ሰርገኛ ጤፍ በሄክታር ከ20 እስከ 30 ኩንታል፣ ማሽላ፣ ገብስ፣ በቆሎ እና ሽንኩርት በሄክታር ከ30 እስከ 60 ኩንታል እንደየ ሰብሉ አይነት ያገኙ እንደነበር የገለጸችልኝ የራያ ቆቦ ተወላጅ የሆነችውና የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ጥናት ተቋም የ3ኛ ዓመት ተማሪ የሆነችው መሰሉ አርብሲ ናት፡፡ ድርቁ የተከሰተው የራያ ቆቦ ገበሬ በበልግ ወራት ይዘንብ የነበረው ዝናብ ሳይዘንብ ሲቀር ሁሉም የክርምቱን ዝናብ በጉጉት መጠበቅ ጀመረ፡፡ ጊዜውም ከወር ወር እየተሻገረ የሐምሌ ወር ገባ፡፡ የሐምሌ ወር በአብዛኛው በኢትዮጵያ አካባቢዎች ዝናብ በጣም የሚዘንብበት ወቅት ነው፡፡ በራያ ቆቦ መሬት ላይ ፊቱን አዞረበት፡፡ የራያ አርሶ አደር ለሊትም ሆነ ቀን ወደ ሰማይ መመልከት ብቻ ሥራቸው ሆነ፡፡ ምን ይደረግ እንግዲህ እንደሰው አይከሰስ፣ አይወቀስ፡፡ እርሱ እንደ ቸርነቱ ፊቱን እንዲመልስ ከመለመን ውጭ፡፡ የነሐሴ ወርም እንደ ሰኔ እና ሐምሌ ወር ፀሐይ ብቻዋን በነፃነት አምርራ ጨረሯን እየለቀቀች ጭካኔዋን አሳረፈችባቸው ምንም የዝናብ ጠብታ ሳይታይ ወቅቱ አለፈ፡፡ አርሶ አደሩም ተስፋ ቆረጠ፡፡

ይቀጥላል!

ፈጣን መረጃ

## በ2008 ዓ.ም በውጭና በሀገር ውስጥ በመመሥረት ላይ ያሉ ግንኙነቶች

| Partnerships on progress | |
|---|---|
| 1 | University of Ferrara |
| 2 | Cankiri Karatekin University |
| 3 | University of the Free state |
| 4 | Royal Institute of Technology (KTH) |
| 5 | Alliance Francis (Addis Ababa) |
| 6 | University of Dar Es salaam |
| 7 | Metech Engineering |
| 8 | Indian Center for Cultural Relations (ICCR) |
| 9 | FAWE |
| 10 | The National University of Singapore |
| 11 | Peking University |
| 12 | University Erfurt |
| 13 | University of West of Scotland |
| 14 | Keio University |
| 15 | The University of Tokyo |
| 16 | Master Card Foundation |
| 17 | Delft University of Technology |
| 18 | University of Nairobi |
| 19 | Korea Institute of Science and Technology |
| 20 | Oromia National Regional State Government Communication Affairs Office |
| 21 | Meles Zenawi Leadership Academy (MZLA) |
| 22 | Amhara Plan Commission |
| 23 | Syracus University |
| 24 | Kassel University |
| 25 | Amhara Design Works Supervision Enterprise (ADSE) |
| 26 | University of Skovde |
| 27 | The Hong Kong University of Science and Technology |
| 28 | Kyoto University |
| 29 | National Higher Institute of Science and Technology-Chad |
| 30 | University of Ndjamena |
| 31 | University of Nebraska - Lincoln |
| 32 | Rhodes University |
| 33 | UCSC- Italy |
| 34 | United State International University Africa-Kenya |
| 35 | Sebles Maret University |
| 36 | University of Khartoum |
| 37 | Federal Government Communication Affairs Office (FGCA) |
| 38 | Ethiopian Broadcast Authority (EBA) |
| 39 | Information Transformation Group |
| 40 | Kyushu Institute of Technology |
| 41 | Society for the Promotion of Museums in Ethiopia |
| 42 | AGH University of Science and Technology |
| 43 | University of Luven |

# ህልም እልም

ቤተልሄም ሃይለማርያም

2ኛ አመት ኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል ተማሪ

www.Facebook.Com /Betelhem Hailemareyam

የቤቱን ማዕዘን ተከትሎ ቁልቁል ከተሰነጠቀው ግድግዳ ፊትለፊት ቆማ አራት ቦታ በተሰነጠቀው መስታወት ጠይም ፊቷን ትመለከታለች:: ቆንጆ ናት፣ ጠይም አሳ መሳይ፣ አይኖቿ የንጋት ኮከብ የመሰሉ፣ጥርሶቿ እንደ ነሃሴ በረዶ የነጡ፣ ከንፈሯ የበሰለ እንጆሪ የመሰለ፣ አፍንጫዋ. . . ቆንጆ ናት:: አንገቷን መለስ ቀለስ ቀና ደፋ እያደረገች በተሰነጣጠቀው መስታወት ውብ ፊቷን ትመለከታለች:: መሰታወቱን ደጋግማ ስትመለከተው አራቱ ስንጥቆች የህይወቷን ግልባጭ፣ የተስፋዋን ንቃቃት የሚያሳብቅ፣ የተቆራረጠ ምኞቷን እያደመጠ የሚደግምላት በቀቀን፣ የምኞቷን ብጫ ሳይሆን የስኬቷ ለሊት ሳይነጋ መጨለሙን የሚያረዳ መልክተኛ መሰላት. . . ፈራች፤ መስታወቱንም ፈራችው:: እየቆራረጠ በሚያሳያት ጠይም ፊቷ ላይ ላይመለሱ የሚያልፉ ቀኖቿ በትዝብት የሚያሾፉባት መሰላት:: አንድ ቀን መሽቶ በነጋ ቁጥር ወደ አለመኖሯ ባንድ እርምጃ መቅረቧን ባሽሙር የሚነግራት መሰላት:: አራቱ ስንጥቆች የውድቀት፣ የመረሳት፣ የመገለል፣ የውርደት. . . ምሳሌዎች መሰሏት:: መስመሮቹ ጥፍራቸውን አሹለው፤ አይናቸውን አጉረጥርጠው ሊውጧት የከበቧት አናብስት ሆኑባት:: መስታዎቱ መልሶ በሚያሳያት ጠይም ፊቷ ውስጥ የተስፋዋን መቀበር ሊያበስራት የተዘጋጀ መሰላት:: “. . . አይሆንም!” አለች ለሷ ብቻ በሚሰማ የዛቻ ድምፅ:: “አይኔ እያማ እራሴን ለሽንፈት አልሰዋም” ስንጥቆቹን ለመሸሸ ሞከረች:: መስታወቱም ካረጀው ኮመዲና ላይ ወርውራ ወደ ውጪ ተጣደፈች. . . ቢሆንም ህሊናዋ ላይ ከተፈጠሩት የሽንፈት ስንጥቆች ማምለጥ አልቻለችም:: እንደ ጤዛ ታይቶ ከጠፋው ክብሯ ጋር ሙግት ገጠመች:: ትናንት ዝነኛ ነበረች በተጭበረበረ የውድድር ውጤት፤ ትናንት ተወዳጅ ነበረች የሷ ባልሆነ ተሰጥኦ ዛሬ ግን ጊዜ አንቅሮ የተፋት የዘመን ትራፊ ናት፤ ዛሬ ግን መረሳት ያጠላባት የታሪክ ልቃሚ ናት፡ ዛሬ ግን. . . አስታራቂ ሽማግሌ፤ ፍርድ ሰጪ ዳኛ በሌለበት የህሊናዋን ክስ መቋቋም አልቻለችም:: የፀፀት ወላፈን ሁለመናዋን ሲያቃጥላት ይሰማታል:: አንጎሏ ውስጥ የተፈጠሩት ስንጥቆች ዙሪያዋን ከበው እንደ አጋም ሲጠበስቋት ይሰማታል:: በማን አለብኝነትና በደም የተነከረችበት ዝና እንደ ደራሽ ጎርፍ መተንፈሻ አሳጥቶ ሲያነገላታት ተሰማት:: ይህ ሁሉ ቢሆንም ግን እስከ መጨረሻዋ ውድቀት ድረስ እጅ እንደማትሰጥ እየፎከረች ህሊናዋን ልታባብለው ትሞክራለች:: “በሃቅ ላይ ተረማምጄ ከወጠሁበት ማማ ማንም አንከባሎ አያወርደኝም” ትላለች:: ህሊናዋ ግን ሽንገላዋን ማመን የሚፈልግ አይመስልም:: “አጨልምሻት ያለፍሻት እውነት የጊዜን ጀምበር ተከትላ የማትፈካ ይመስልሻል?. . . ሲያምርሽ ይቅር ባንቺ ምክንያት ያለቀሱ ዓይኖቿ እንደራሄል እንባ ፀባኦት መድረሻቸው ቀርቧል፤ ባንቺ ምክንያት መና የቀረው ላብ እንደ አቤል ደም ወደ አርያም እየጮኸ ነው፤ ባንቺ ምክንያት የተፈጠሩ ጠባሶች. . .” ይላታል:: ከዚህ በላይ የቅሌቷን ክስ ማዳመጥ አልፈለገችም:: ኡ. . ኡ. . ኡ. . ብላ መጮህ አማራት:: ከሷ በፊት ግን ተፈጥሮ በሷ ላይ የጮኸች መሰላት:: ከበላይዋ ያለው ስማይ፣ ከቆመችባት ምድር፣ ፀሃይና ንፋስ፣ አፈርና ውሃ፣ ሁሉም ተፈጥሮ ላንቃው እስኪበጠስ ከእዮር እስከ ራማ በሚያስተጋባ ድምፅ የሚጮህባት መሰላት:: ካለም ህዝብ ተለይታ ለሷ ብቻ የምፅኣት ቀን የመጣ መሰላት፣ የመጨረሻው የውድቀት እንቢልታ ተነፋ፣ የመጨረሻው የሽንፈት ነጋሪት ተጎሰመ፣ እውነት በግርማ መጥታ እሷን በግራ አያቷን በቀኝ አቁማ ታቦር ተራራ ላይ ለፍርድ የተሰየመች መሰላት:: በግራ እጇ ደረቷን ዳበሰች

ትናንት ዝነኛ ነበረች
በተጭበረበረ የውድድር ውጤት፤
ትናንት ተወዳጅ ነበረች የሷ ባልሆነ
ተሰጥኦ ዛሬ ግን ጊዜ አንቅሮ የተፋት
የዘመን ትራፊ ናት፤ ዛሬ ግን መረሳት
ያጠላባት የታሪክ ልቃሚ ናት፡ ዛሬ
ግን. . .

ልቧ ባፌዋ ልትወጣ ይመስል እንደ ፅጌ ከበሮ ትደለቃለች:: ኤርታሌ ብብቷ ስር የፈነዳ እስኪመስላት ድረስ የሰውነቷ ሙቀት ይፈጃት ጀመር:: “ ኦ . . . ኦ . . . አምላኬ እያበድኩ ነው እንዴ!?” ክህደቷ ተጠራቅሞ እንደ አሪምስ አንጀቷ ተዘርግፎ እንዳትሞት የፈራች ይመስል ሆዷን በሁለት እጇ እቅፍ አደረገች:: “ኤ . .ኤ. . .ሎ. . . ሄ. . . ኤሎሄ” የቤቱ ስልክ “ሲርርርርርር” አለ:: በድጋሚ “ሲርርርርርርር . . “ ካልጋዋ ላይ ተስፈንጥራ ወረደች:: ህንድ ውቅያኖስ ገብታ የመጣች እስኪመስል ድረስ ሁለንተናዋ በላብ ርሷል፤ ቡናማ የለሊት ልብሷ ከሰውነቷ ተጣበቋል፤ ፀጉሯ በላብ የወረዛ ፊቷ ላይ ተለጣጥፏል:: “ሲርርርርርር” ስልኩ ለስድስተኛ ጊዜ እየተንጫረረ ነው:: አነሳችው “ሄሎ ጤና ይስጥልኝ አርቲስት ኤልሳቤት?” አላት ጎርናና የሌሊት ድምፅ::

“አ . . . ዎ” ቃሉ ደም ደም አላት “ነ. . . ኝ” ማ ልበል?” በግራ እጇ እያማተበች ነው::

“ከሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ነው የምድውለው:: አያትሽ . . .” ከዚህ በላይ የመስማት አቅም አላገኘችም፤ ስልኩን ለቀቀችው. . .

ይቀጥላል!

# ነግበኔ ...

ከገጽ 12 የዞረ

አየች:: 2:45 ሆኗል:: ቤቷን ቆልፋ ወጣች::

የደበረብርሃን ከተማ ከጠዋት ቆፈን አልተላቀቀችም:: ፀሃይ ደብረ ብርሃንን ከቅዝቃዜ ለማላቀቅ እየታገለች ነው:: ነዋሪዎቿ የቻሉት ለብርዱ ፍቱን ነች ያሏትን “ብልጧ” ወይም “ያንበሳ ወተት” ብለው የሚጠሯትን አረቄ ቀመስ አርገው፤ ሌሎቹም ግራ ቀኝ እጃቸውን አፋትገው፤ የተቀሩትም ወፍራም ወፍራሙን ለብሰው ራሳቸውን አሙቀው እንደፀሃይዋ ከተማዋን ለማሞቅ እየታገሉ ነው:: ሄለን በከተማዋ እንብርት ላይ የተገነባው ደብረ ብርሃን ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን በር ላይ ቆማ ተሳለመች:: ነጠላ የለበሱ ምእመናን ይገባሉ፤ ይወጣሉ:: ደብርብርሃን ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን፤ ቤተክርስቲያን ከመሆኑ በፊት አባ በርሶማ የወንዶች ገዳም ይባል እንደነበር፤ ደብረ ብርሃን እራሷ እንደዛሬው ቀዝቃዛ ከመሆኗ በፊት እባብና ዘንዶ የሞላት በርሃ እንደነበረች፤ እባቡ ቤተመቅደስ ድረስ እየገባ ያስቸግር ስለነበር አፄ ዘርዓያዕቆብ በረሃማዋን ከተማ ደጋ፣ እባቡንም ገዝተው ከተማ እንዳይገባ እንዳደረጉ ተቋመወርቅ የተባሉ የቤተክርስቲያን ሊቅ የአፄ ዘርዓያዕቆብንና የደብረብርሃንን ታሪክ በሚያትተው መጽሃፋቸው ገልፀዋል::

ሄለን ከቤተክርስቲያኑ በስተቀኝ ወደ ሚገኘው ሜላት ካፌ ስትገባ ኤልያስ ብቻውን ተቀምጦ ጠረንጴዛ ላይ የፈሰሰ ውሃ በጣቱ እያጠቀሰ ጠረንጴዛው ላይ ይፅፋል:: ሳያያት ተጠግታ የፃፈውን አነበበችው:: በጣም ተናደደች:: ደሟ ፊቷ ላይ ሲሯሯጥ በቅፅበት የተቆጣ ነብር መሰለች::

“ምንድነው እሱ!” አምባረቀችበት::

“ፅሁፍ ነዋ!” ከየት እንደመጣች ስላላያት ደንግጧል::

“ምንድነው የሚለው”

“ህይወት ውሻ ናት!! ሄሊዬ አፈቅርሻለሁ ነዋ::”

“አረ ባክህ ትወደኛለህ!! ነገ እኔንም እንደእሷ በየቦታው ስትሰድበኝ አገኝሃለሁ::”

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# የግጥም ጥግ

## እርግጥ ነው

ባህር ቢደፈርስ አልያም ቢሸተው
ጥዩፍ ቢሆንበት ምንም ባይመቸው
አሳ ወጥቶ አይሄድም አይኖርም በሜዳው
ከህዝቡ አኗኗር ካደገበት ልማድ
አንድ ሰው ለብቻው አፈንግጦ ቢሄድ
ትክክል ቢሆንም የእርሱ ፍልስፍና
‹‹እብድ ነው›› ይሉታል ብቻውን ነውና::

## የኔ ጀግና

ጊዜው ተመችቶት ወንበሩን አግኝቶ
አጋጣሚው ሁሉ ለእርሱ ተመቻችቶ
ያሻውን ለማድረግ ያሻውን ለማፈስ
አንዱን ለመግንባት ሌላውን ለማፍረስ
እማኝ በሌለበት ዳናውን አጥፍቶ
ብዙ ለመሰብሰብ ሁኔታ ተቃንቶ
በትከሻው ታምኖ እህቱን ወንድሙን
አክስት አጎቶቹን ዘመድ አጋሮቹን
እየሰባሰበ ጎጡን ከያለበት
ሥፍራ መስጠት ሲችል በተገኘው ክፍተት
እርሱ ግን ......
ለህሊናው አድሮ እውነትን ተላብሶ
ሀገሩን ኢትዮጵያን በልቡ አንግሶ
ሽፍጥና ምዝበራን እጅግ ተፀይፎ
እራሱን ለሌሎች ከተሰጠ ታልፎ
ጊዜውን ወንበሩን ለህዝቦች አዳራ ከተጠቀመበት
አርዕያ ለትውልድ ይህ ነው ጀግና ማለት
ለኢትዮጵያ ህዳሴ የታሪክ ባለቤት (ወደፊት)::

በደስታ ተከስተ (ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፀጥታ አገልግሎት)

# የምክርና ድጋፍ አገልግሎት አስፈላጊነት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

በትዕግስት ዳዊት

የምክር እና ድጋፍ አገልግሎት (Guidance & counseling service) የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (UN) ምክር እና ድጋፍ (Guidance & counseling) በሚለው መመሪያ ጽሁፍ ላይ ግለሰቦች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እቅድ እንዲያወጡና ባላቸው አቅምና ችሎታ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ እንዲሁም በውሳኔያቸውም መሰረት ፍላጐታቸውን ከሕብረተሰቡ ፍላጐት ጋር በማጣጣም መኖር እንዲችሉ የሚረዳ ሳይንሳዊ መሳሪያ ነው፡፡

ምክርና ድጋፍ በተለይ በትምህርት ቤት አካባቢ ተማሪዎች

- የተሻለ ትምህርት እንዲቀስሙ
- ጥናትና ምርምር እንዲያካሄዱ
- የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ
- የራሳቸውን ችሎታና አቋም እንዲገመግሙ
- ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ
- የራሳቸውን ፍላጐት እንዲለዩና የወደፊት አላማቸውን እንዲተልሙ እንዲሁም መዋቅር እንዲዘረጉ የሚረዳ የአመራር ስልት ነው፡፡

ምክርና ድጋፍ በማንኛውም የእድሜ ክልል ለሚገኝ ሰው የሚሰጥ አመራር ሲሆን የተለያዩ ክፍሎች አሉት፡፡

1. የትምህርት አመራር (Educational Guidance)
2. የባሕሪ አመራር (Behavieral Guidance)
3. የሙያ አመራር (Vocational Guidance)

ምክር (Counseling)

ማማከር የምክርና ድጋፍ አገልግሎት አንዱ ክፍል ሲሆን በሕግ፣ በጤና ወይም በፖለቲካ አማካሪዎች የተለያየ ትርጉም የተሰጠው ቢሆንም በሳይኮሎጂ ግን ለየት ያለ ትርጉም ያለውና ብዙውን ጊዜ በግለሰቦች ላይ ያለውን የግል ችግር ማለትም የመንፈስ ጭንቀት፣ ማሕበራዊና ትምህርት ነክ ችግሮች፣ የስሜት ቅራኔዎች እንዲሁም የባህሪይ ቀውስና የመሳሰሉትን እንደየሁኔታው በግልም ሆነ በቡድን ችግሮችን ለማቃለል የሚሞክርበት ሳይንሳዊ ዘዴ ነው፡፡

ማማከር ከአንዱ ወደሌላው የሚሰጥ ምክር ሳይሆን ከምክር በላይ ነው፡፡ አገልግሎቱም የሚሰጠው በሰለጠነ ባለሙያ ሆኖ በሥነ ባህሪይ ቀውስ ለተጠመዱ ብቻ ሳይሆን በእቅድ የመመራት ችግር ላለባቸው ጭምር ነው፡፡ ማማከር የግንኙነት ሂደት ሲሆን በውስጡ በርካታ ተግባራት እንደሚከናወኑ ምሁራን ይናገራሉ፡-

1. እርዳታ ተቀባይ (client) ወደፊት ተመሳሳይ ችግሮች ቢያጋጥሙት በራሱ ችሎታ ችግሮችን ማቃለል እንዲችል ይረዳል፤
2. አማካሪው የችግሩን መንስኤና መፍትሄ ተገንዝቦ ደንበኛውን (client) የሚያግዝበት ሂደት ነው፤
3. የደንበኛውን ሁለንተናዊ ባሕሪ ለውጥ ለማጐልበት በታመነ መስመር ላይ የሚካሄድ እንቅስቃሴ ነው፤
4. አማካሪ ባለሙያ (councilor) የደንበኛውን ችግር ተገንዝቦ ቁርጥ ያለ ውሳኔ እንዲወስኑ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ነገር ግን አማካሪው የመወሰን ሀላፊነት የለውም፤ የመወሰን ሀላፊነት ያለው ራሱ ባለጉዳዩ (client) ነው፤
5. ማማከር አመች ይሆናል ተብሎ በተገመተበት ቦታ ሁሉ ይካሄዳል፡፡

የምክር እና ድጋፍ አገልግሎት አስፈላጊነት በከፍተኛ ትምህርት ተቋም

- ❖ ትምህርት ቤቶች የአዲስ ሀሳብ ማመንጫ ስፍራዎች በመሆናቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለና እየጨመረ የመጣውን የሰው ልጅ አስተሳሰብ መሰረት በማስያዝ ተማሪዎችን ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የራሳቸውን ችሎታና ፍላጐት ለማጣጣም እንዲችሉ የተጠናከረ አመራር መስጠት በማስፈለጉ፤
- ❖ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እያደገ የመጣ በመሆኑ በዚሁ የቴክኖሎጂ እድገት አኳያ አዳዲስ የተፈጠሩ የትምህርትና የስራ መስኮች በተማሪዎችም ሆነ በወላጆች ስለማይታወቁ በፅሁፍም ሆነ በቃል ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤
- ❖ በአሁኑ ጊዜ ወደ ኮሌጆችና ልዩ ልዩ የሙያ ትምህርት መስጫ ፕሮግራሞች የሚገቡ ተማሪዎች ቁጥር ከበፊቱ ጋር ሲነፃፀር እጅግ በርካታ በመሆኑ እያንዳንዱ ተማሪ ሀገሪቱ የምትፈልገውን ስራ ለመስራት እንዲችል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤
- ❖ ጤናማ የሆነ ትውልድ ማፍራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤
- ❖ ከሱስ ነፃ የሆነ ትውልድ ማፍራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤
- ❖ የመማር ማስተማር ሂደት ጥሩ በሆነ መልኩ መጓዝ እንዲችል በማስፈለጉ፤
- ❖ በአጠቃላይ ተማሪዎች ካለው ስርዓተ ትምህርት ጋር እራሳቸውን አጣጥመው ስኬታማ በሆነ መልኩ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡

አገልግሎቱ የሚያተኩርባቸው ጉዳዮች እና ዋና ዋና ችግሮች

1. በአጠናን ችግር (Study Problem)
2. በትምህርት መድከም (Academic weakness)
3. የመጨነቅ ያለመረጋጋት ስሜት (Stress)
4. አካባቢን የመልመድ ችግር (Adaptation problem)
5. የጊዜ አጠቃቀም (Time Management)
6. የበታችነት ስሜት(Inferiority complex)
7. ፆታዊ ትንኮሳ (Harassment)
8. የማንነት ጥያቄ (Identity Problem)
9. በሱስ የመጠመድ ችግር (Substance abuse)
10. የተቃራኒ ፆታ ፍቅር (Opposite sex)
11. ግጭትና አለመግባባት (Conflict and disagreement)
12. ሀሳብን በነፃነት መግለፅ (presentation problem)
13. የአእምሮ መታወክ (Mental illness)
14. ድብርት (Depression)
15. በራስ ያለመተማመን ችግር (lack of self confidence)
16. የትምህርት እና የስራ ጫና ችግር

ከባለጉዳዩ (Client) የሚጠበቁ ዋና ዋና ነገሮች

- ችግሩ ከመባባሱ በፊት ወደ ምክር አገልግሎቱ መምጣት
- ለአማካሪው ግልፅ መሆን
- ለውሳኔ ቅርብ መሆን
- ከአማካሪዎች የውሳኔ ሐሳብ አለመጠበቅ
- ሀሳብን በነፃነት መግለፅ
- የቀን ቀጠሮ ማክበር

‹

ከአማካሪው (Counselor) የሚጠበቁ ዋና ዋና ነገሮች

- ✓ ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉበትን የአጠናን ዘዴ ያማክራል፡፡
- ✓ የማሕበራዊ፣ የፖለቲካዊ እና የስነልቦ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ተቀብሎ ከችግራቸው እንዲላቀቁ የአመራርና የምክክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- ✓ ተማሪዎች ተገቢ የሆነ ባሕሪ ይዘው እንዲጓዙ የአመራር አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- ✓ ተማሪዎች ከወላጅ እርቀው በሚኖሩበት ጊዜ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮችና ፈተናዎች ያሳያል፡፡
- ✓ ተማሪዎች በአገሪቱ ውስጥ ስላሉ የስራ መስኮች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው መረጃ በመስጠት ለወደፊት ስነልቦናዊ ዝግጅት እንዲኖራቸው ይረዳል፡፡
- ✓ ተማሪዎች ጥናትና ምርምር እንዲያደርጉና እንዲሁም የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛል፡፡
- ✓ በዕቅድ የመመራት ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች የአመራርና የምክክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- ✓ ችግር ያለባቸውን ብቻ ሳይሆን ጤነኛ ሆነው ኑሮንና ስራን የመምራት ችግር ያለባቸውን የአመራርና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- ✓ ባለጉዳዮች እንደአስፈላጊነቱ ከተለያዩ የስራና የትምህርት ክፍሎች ጋር ያገኛል፤ እንዲሁም አቅጣጫ ይጠቁማል፡፡
- ✓ የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት የሚታገዝበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡
- ✓ በክፍል ውስጥ፣ በቤተመፅሐፍት፣ በመመገቢያ አዳራሽና በመሳሰሉት የስራ ክፍሎች ተገቢውን ስነ ስርዓት አክብረው እንዲኖሩ ምክር ይሰጣል፡፡

# ፎቶ ማህደር

የኢፌዲሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስትር ዶ/ር ከስተብርሃን አድማሱ፣ የአብክመ ጤና ጥበቃ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ብዙአየሁ ጋሻው፣ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮች ፈለገ ህይወት ሆስፒታልንና ዩኒቨርሲቲው እያሰራ ያለውን የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ስፔሻላይዝድ ማስተማሪያ ሆስፒታልን ሲጎበኙ














